# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ደ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

# ትንሣኤ



«የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት »

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም
ቁጥር 52
ጥር ፲፱፻፸፬ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራዶ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ትምህርተ ሥጋዌ | ፪ |
| ጥምቀት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት | ፬ |
| ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ | ፮ |
| የሲዳማ ብሔረ ሰብእ ባህል | ፰ |
| ትምህርተ ግእዝ | ፱ |
| አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ | ፲ |
| የድርሰት አዳዳፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፲፩ |
| የአልኮል መጠጥ ጐጂነት | ፲፫ |
| ሥርዓተ ጸሎት | ፲፬ |
| ነፍስ ጡር ሴቶች | ፲፮ |
| የነፃ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን | ፲፰ |
| የአባለ ዘር በሽታ | ፲፱ |
| እናንተ የምድር ጨው ናችሁ | ፳ |
| ድንግል ማርያም በቃና ዘገሊላ | ፳፩ |
| ወጣት መነኮሳት | ፳፫ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከዚህ በታች የማቀርበውን ጥያቄ አብራርታችሁ እንደምትመልሱልኝ እተማመናለሁ ።

በሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ተዓምረኛ ቤ/ክርስቲያን አለ ሲባል ሰምቻለሁ ። ይህ ቤተ ክርስቲያን በላይ ጣራ የለውም ። ዝናም አያስገባም ግን የፀሐይ ብርሃንን አይከለክልም ይባላል ። የዚህን ቤተ ክርስቲያን ሙሉ አድራሻና እንዴት ዝናም እንደማያስገባ እንድትገልጡልኝ እፈልጋለሁ ።

መዝገቡ ገለቱ
አዲስ አበባ

መዝገቡ ገለቱ ስለ ጥያቄዎ እጅግ እናመሰግንዎታለን ። ለማወቅ የፈለጉት ቤተ ክርስቲያን በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ በሙቄት ወረዳ የሚገኝ የአቡነ አሮን ቤተ ክርስቲያን ነው ቤተ ክርስቲያኑ ከቋጥኝ ተፈልፍሎ ተሠርቷል ። ጣራውም ግድግዳውም ከቋጥኝ የተፈለፈለ መሆኑን በታውን ያዩትና ለብዙ ጊዜ የኖሩበት ሰዎች ያስረዳሉ ። አዘጋጁውም ያዩትን ሰዎች አነጋግሮአል ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በቅኔ ማኅሌቱ አንፃር በጣራው ላይ ቀዳዳ አለ ። የቀዳዳው ስፋት በሜትር ሦስት በሦስት ነው ። ይህም ዘጠኝ ስኩዌር ሜትር መሆኑ ነው ።

ይህን ያህል ስፋት ሲኖረው በክረምት ጊዜ ዝናም አያፈስም ። ግን የፀሐይ ብርሃን ብቻ ይገባል ። ከታች በቀዳዳው አንፃር መጽሐፍ ተዘርግቶ ይነበባል ። ታዲያ አንዳችም የዝናም ጠብታ በመጽሐፍ ላይ አይታይም ። ተአምር የሚያሰኘውና የሚያስደንቀውም ይህ ነው። ይህም የሆነው በአንድ አይነት ዘዴ ሳይሆን መልዕልተ ተፈጥሮ በሆነ ተአምር ነው ። ይህንም የውስጥና የውጭ ሀገር ሰዎች ሁሉ በዓይን አይተው አረጋግጠዋል ።

የአቡነ አሮን በዓል በመስከረም 5 ቀን ይከበራል ። በዚህ ዕለት ከአሥራ አራቱ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ብዙ ምእመናን ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ ። መስከረም የዝናም ወር እንደመሆኑ መጠን ዝናም ሲጥል የሄዱት ምእመናን ሁሉ በውስጥና በውጭ እየሆኑ የጣራው ቀዳዳ ዝናም አለማፍሰሱን ይመለከታሉ ።

በዚሁ ዕለት ከተለያዩ አድባራት የሚሄዱ ሊቃውንት የዚህን ቤተ ክርስቲያን ተአምራታዊነት በየጊዜው በቅኔያቸው ገልጠዋል ። ለምሳሌ የተድባበ ማርያም ሊቅ ቀኝ ጌታ መኩብብ ከዚህ በሚከተለው መወድስ ቅኔ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ እንዲህ ብለዋል ።

መምህረ ሥርዐት አዘዝከ በከመ ይደሉ

በስቁረተ መቅደስ ኢይብእ
ነጥበ ማየ ክረምት ሞአባዊ
አንተኑ ኤልያስ
እስከ ይብለከ ለባዊ ።
በዊእ እምኀበ ይለዎ
ለብርሃን ሌዊ
ወለእመ አሮን ደኃራዊ
ልምላሜ አዕባን መጠንከ
በአቅመ በትረ አሮን ቀዳማዊ ።
ለአዳምሂ ፀሐየ ጽድቅ
ዘተፈጥሮቱ ላዕላዊ ።
በዊአ መቅደስ ትቀድሞ
አሮን ፊያታዊ
ወበተሐድሶ ሀለወ
እንዘ ውእቱ ማሕየዊ ።
ዝናም ዘየኀፍሮ
ሕንፃ መቅደስከ አረጋዊ ።

ቀኝ ጌታ መኩብብ በብሉይ ኪዳን ሕግ ወደቤተ መቅደስ ስለሚገቡና ስለማይገቡ ወገኖች የተሰጠውን ሥርዐት በመጥቀስ ስለ አቡነ አሮን ቤተ ክርስቲያን ተቀኝተዋል ። የሞአብ ወገን ወደ አይሁድ ቤተ መቅደስ እንዳይገባ በሙሴ ሕግ ተከልክሎ ነበር ። ይህን ድርጊት በአሮን ቤተ መቅደስ ዝናም በአለመግባቱ መስለውታል ። ቀጥለውም ነቢዩ ኤልያስ ለሦስት ዓመታት ከስድስት ወራት ዝናም እንዳይዘንም ያደረገውን ታሪክ አቡነ አሮን ጣራው ክፍት በሆነ ቤተ ክርስቲያናቸው ዝናም እንዳይገባ ካደረጉት ተአምር ጋር አነፃፅረውታል ። በብሉይ ኪዳን ሕግ የሌዊ ወገንብቻ ወደ ቤተ መቅደስ እንዲገባ መፈቀዱን ደግሞ የፀሐይ ብርሃን በቤተ ክርስቲያኑ የጣራ ቀዳዳ ውስጥ ከመግባቱ ጋር ማወዳደራቸውን የቅኔው ሦስተኛ ቤት ያሳያል ።

በመጨረሻ ሊቁ "እገሌ ዝናም የሚያፍረው ሽማግሌ ነው » በሚለው ኢትዮጵያዊ የአባቶች አነጋገር በመጠቀም

ዝናም የሚያፍረው የመቅደስህ ሕንፃ ሽማግሌ ሁልጊዜ በተሐድሶ ይኖራል፡ በማለት የአቡነ አሮን ቤ ክርስቲያን በክረምት ዝናም የማያፈስ ብርሃን ብቻ የሚያስገባ መሆኑን ገልጠዋል ። ሌላው ባለቅኔ ደግሞ ስለዚሁ ተአምራዊ ቤተ ክርስቲያን ሲቀኝ

''ገብሩ ተራድኦ
ካህን አሮን
ለመቅደስከ ዐባይ
ዝናም በአፍአ
ወበውስጥ ፀሐይ ........''

ካህን አሮን ሆይ ለታላቅዋ መቅደስህ ዝናም በውጭ ፀሐይም በውስጥ አገልግሎት አደረጉ ብሏል ።

ታላቁ ሊቅ አለቃ ለማ የተወለዱ በሙቄት በአቡነ አሮን ደብር ነው ። ሰድሚያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ጐጃም ወጥተዋል ። ከጎጃምም በቀጥታ ወደአዲስ አበባ መጥተው እንደገና ወደ ትውልድ ሀገራቸው ሳይገቡ በአዲስ አበባ ኖረዋል ። ይህን በማስመልከት የተቀኙት ቅኔ እነሆ

ተከታዩን በገጽ ፱ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ትምህርተ ሥጋዌ

ሥጋዌ ማለት ሰው መሆን ማለት ነው ። ይህም ቅድመ ሥጋዌ አለሥጋ በሌላ መልክ ለነበረ አካል እንጂ በመጀመሪያ በሥጋ አካል ለኖረ የሚነገር ቃል አይደለም ።

አስቀድሞ በመንፈሳዊ አካል የነበረው ሕያውና እውነተኛ አምላክ በዘለዓለማዊ ልደት ከአብ አለተድኅሮና አለተከፍሎ የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆነ ።

የአምላክ ሥጋዌ ( ሰው መሆን ) ያስፈለገበት ምክንያት ሰው በኃጢአት በወደቀበት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ ሰውን እንደሚያድን የተስፋ ቃል ተናግሮ ስለነበር ነው ። ነገር ግን ሥጋዌው እግዚአብሔር ራሱን እንደገለጠባቸው አንዳንድ አጋጣሚ ነገሮች አይደለም ። ሰው ኃጢአት ባይሠራም ኖሮ እንኳ « አምላክ ስለ ፍቅሩ ሰው ይሆን ነበር » እንደሚለው እንደ አንዳንድ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት ፍልስፍናም አይደለም ።

ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ለምን ተወለደ? በማለት ከጠየቀ በኋላ እንደሚከተለው ይመልሳል « እግዚአብሔር ሰው በመሆን ተወልዶ በሰዎች መካከል የተገኘበት ምክንያት ይህ ነው ። የሰው ባሕርይ በኃጢአት በሽተኛ ስለሆነ ዶክተር ይፈልግ ነበር ። ሰው ወድቆ ነበር ስለዚህም ከወደቀበት የኃጢአት ዐዘቅት የሚያነሣው ይሻ ነበር ። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ነበረው ግን ያ ግንኙነት ተቋርጦበት ነበርና አገናኝ አስፈለገው ። በኃጢአት ጨለማ ውስጥ የነበረው ሰው ወደ ብርሃን የሚያወጣው አንድ ኃይል ማግኘት ያስፈልገው ነበር ሰው በኃጢአት ሰንሰለት ታስሮ በሰይጣን ፈቃድ ተማርኮ ለሰይጣን ተገዥ ሆኖ ይኖር ነበር ። ስለዚህ ከሰይጣን ተገዥነት የሚያወጣው ለማግኘት ተስፋ ያደርግ ነበር ። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ እንደዚህ ስለሆነው ሰው ከሰማያት ወረደ ፤ ከድንግል ማርያም ተወለደ ።

ሰው አስገኝ ወይም ፈጣሪ በሌለው በባዶ ዓለም ውስጥ ራሱን ከሁሉ በላይ ፈጣሪ አድርጎ የሚኖር እንዳይደለ ግን ከርሱ በላይ እግዚአብሔር እንዳለ እግዚአብሔር ራሱም ከሰው ጋር እንደሆነ ለማረጋገጥ ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ ። ስሙም እግዚአብሔር ከእኛ ( ከሰዎች ) ጋር ተባለ ።

የእግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መምጣት በዓለም ውስጥ የአስተዳደር ሕግ ለመሥራትና ፍልስፍና ለማስተማር አይደለም ። በመልካም ምክር ብቻም ዓለምን ለማዳን ወደ ዓለም አልመጣም ። ለምሳሌ ሸክሙ የከበደውን ሰው ሸክሙን እንዲጥልና ዕረፍት እንዲያደርግ መምከሩ ቀላል ነው ። ነገር ግን ሸክምህን እኔ ልሸከምልህ ማለት እጅግ ከባድ ነው ። ስለዚህ እግዚአብሔር ወልድ የራሱን ሕይወት ስለሰዎች ቤዛ በመስጠት ሰዎችን ለማዳን ወደዚህ ዓለም መጣ ።

ሰው ምንም እንኳ በኋላ ኃጢአተኛ ቢሆንም በፈጣሪው ዘንድ እጅግ የተወደደ ፍጡር ነው ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረ ስለሆነ በፈጣሪው ዘንድ የተከበረ ነው ። ይህ የተወደደና የተከበረ ፍጡር በኃጢአት እንደተዋረደ ይቀር ዘንድ እግዚአብሔር አልፈቀደም ። ወደ ቀደመ ክብሩ ሊመልሰው ወደደ እንጂ ።

እግዚአብሔር የፈጠራት ምድር መልካም ነበረች ። ነገር ግን በምድር ላይ እንዲኖር በተፈቀደለት ሰው ኃጢአት ምክንያት ምድር ተረግማ ነበር ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለፈጠራት ምድር ይጠነቀቃልና በኪደተ እግሩ ይቀድሳት ዘንድ ሰው ሆነ በምድርም ተመላለሰ ። ምድርም የእግዚአብሔርን የእግሩን ማሕተም አገኘች። ራሱ እንደተጠነቀቀላት ሰዎችም ይጠነቀቁላት ዘንድ አስተምሮአል ።

እግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ሳይሆን አካላዊም ነው ። መሆኑንም ግዙፍ ሥጋን በመዋሐድ ገለጠ ግዙፍ አምላክን ለሚሹ ረቂቅ አምላክ ግዙፍ ሥጋን በመዋሐድና ሰው በመሆን ታያቸው ። እግዚአብሔር ወልድ ሰው ከመሆኑ በፊት አንዳንድ ሃይማኖታውያን ማንኛውም ግዙፍ አካል ክፉ እንደሆነ ያስቡ ነበር ። ለምሳሌ የሰው አካል ክፉ ስለሆነ በጾምና በሌሎች አካልን የማድከም ሥርዐቶች መድከም እንዳለበት ያስተምሩ ነበሩ ። ነገር ግን እግዚአብሔር ወልድ የሰው አካልን ገንዘብ በማድረግ ቀደሰው ። የሰውን አካል ብቻ ሳይሆን ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም በመመላለሱ ዓለምን ሁሉ ቀደሰ ።

እግዚአብሔር ለምን ሰው ሆነ ? ሰው ሳይሆን ማዳን አይችልም ነበር? የሚል የተለመደ ጥያቄ አለ ። አዎ እግዚአብሔር ፈታሒና መሐሪ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። « ትእዛዜን ብትተላለፉ ትሞታላችሁ» ብሎ እንደተናገረ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች በፍርዱ መሠረት ሞቱ ። ከእግዚአብሔር ፊት ተለዩ ። እንግዲህ በመሐሪነቱ እንዳያድናቸው ፍርዱ ይለወጣል ። ሌላ ሰው እንዳያድናቸው ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ሆኖአል ። ከዚህ ላይ ኃጢአት የሌለበት የእነርሱን ፍርድ የሚቀበል ሌላ ንጹሕ ጻድቅ ሰው አስፈለገ ስለዚህ እግዚአብሔር ፈታሒነቱና መሐሪነቱን ጠብቆ እሩይ ማእከለ እግዚአብሔር ወሰብእ በመሆን የእነሱን ፍርድ ሲቀበል በጽድቁ ሰው ሆነ ። ሰውንም አዳነ ። ሮሜ .8.3-4 ። ዕብ . 2፥14.15

ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሲሆን ቅድመ ሥጋዌ የነበረ ባሕርዩ ድኅረ ሥጋዌ አልተለወጠም ። ባሕርየ ትስብእ ትም ድኅረ ተዋሕዶ ባለ መለወጥ ኖረ ።በግልጥ አነጋገር ህላዌ ትስብእትም አልተለወጠም ድኅረ ተዋሕዶ ባለመለወጥ ኖረ ። በግልጥ አነጋገር ህላዌ መለኮት ወደ ህላዌ ትስብእት አልተለወጠም ። በዚህም አንጻር ህላዌ ትስብእት ወደ ህላዌ መለኮት አልተቀየረም ። ጥንት የነበረው ትስብእት ጥንት ያልነበረው መለኮትን በመዋሐዱ ቀዳማዊ ሆነ፡ጥንት ያልነበረው መለኮትም ጥንት የነበረው ትስብእትን ስለ ተዋሐደ ዘመን ተቆጠረለት ።

የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ አለ መደባለቅ አለ ውላጤና አለ ተከፍሎ ነው ። ከዚህም የተነሣ ሥግው ቃል ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው ። አንድ ፈቃድ አንድ ግብር ነው ።

እግዚአብሔር ወልድ በማሕፀነ ድንግል ማርያም ተፀንሶ ሲወለድ፡ዘርአ ብእሲ ምክንያት አልሆነውም። ግን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ተፀነሰ ። በግብረ መንፈስ ቅዱ ስ ተወለደ ። ከዚህ የተነሣ እናቱ ቅድስት ማርያም ዘለዓለማዊት ድንግል ናት ። የክርስቶስ ፅንስና ልደት ተአምራውያን ስለ ሆኑ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ክርስቶስን በወለደች ጊዜ በሴቶች ላይ የማሆነው ልማድ አልደረሰባትም።

ክርስቶስ ያለ ዘርአ ብእሲ መፀነሱና መወለዱ አስቀድሞ የነበረ አምላክ መሆኑን ለማረጋገጥ ና ከሦስቱ ኃይላትም እንዳይደለ ለማስረዳት ነው ። ድንግልናዊ ልደቱም ብዙዎች ሐሰተኞች ክርስቶሶች ስለሚነሡ ከእነርሱ የሚለይበት ምልክት ነው ( ኢሳ . 7 . 14 )

ትምህርተ ሥጋዌን ለመቃወም የተነሡ ብዙ መናፍቃን ሊቃውንት ነበሩ ለምሳሌ አርዮስ "ክርስቶስ አምላክ አይደለም ግን በመጀመሪያ ከሁሉ በፊት የነበረ ፍጡር ነው " ሲል አስተማረ ይሁን እንጂ በ317 (25 ) ዓ.ም ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረትነት ረትተውታል ክርስቶስም ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንደሆነ አስረድተው የሃይማኖት ውሳኔዎችን አጽድቀዋል ።

ንስጥሮስም "ከድንግል ማርያም የተወለደው ሰው ብቻ ነበር ግን አምላክ ቢያድርበት አምላክ ሆነ በማለት አስተማረ ይህም ከህይት ወንጌላዊው ዮሐንስ « ቃል ሥጋ ሆነ » የሚለውን ትምህርተ ሥጋዌ ባለማስተዋል የተመሠረተ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አውግዘው ለይተውታል ።

አውጣኪ የተባለውም መናፍቅ "የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ በውላጤ እንደሆነ ለማስተማር ተነሥቶ ነበር። እርሱም ስህተተኛነቱ ተገልጦ ተወግዞአል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እነዚህንና ሌሎች መናፍቃን ስለ ሥጋዌ አምላክ ያቀረቡትን የተሳሳተ ትምህርት በብሔራዊያን ሊቃውንት ስትከላከል ኖራለች ትኖራለችም ። ነገር ግን እግዚአብሔር ወልድ ከዘለዓለም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዕሪና የነበረ በኋላም ሰውን ለማዳን በራሱና በአባቱ በቅዱስ መንፈሱም ፈቃድ ከቅድስት ድንግል እግዝእትነ ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ሰው ( ሥግው ) እንደ ሆነ አምና ታስተምራለች ።



www.ethiopianorthodox.org

# ጥምቀት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት

ሕገ ወንጌልን የተቀበሉና በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ተጠምቀው የጸጋ ልጅነትን ይቀበላሉ ፡ በወልድ "ውሉድ" በክርስቶስ "ክርስቲያን" ተብለው ይጠራሉ ። የአፈጻጸሙ ሥነ ሥርዓት ግን እንደየአብያተ ክርስቲያናቱ ይለያል ፡

አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ 1ኛ የክርስቶስን በዓለ ጥምቀት እንዴት እንደሚያከብሩ ፡ 2ኛ ለተከታዮቻቸው ሥርዓተ ጥምቀትን መቼና እንዴት እንደሚፈጽሙ ለማወቅ ።

ሀ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ፍራንችስኮስ ገዳም መንፈሳዊ ኮሌጅ ኃላፊ አባ ሙሴ ገ ጊዮርጊስን

ለ በኢትዮጵያ የእንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ቄስ ኮሊን ባትልን

ሐ በኢትዮጵያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ፋዘር ኒክታርዮስን ቤተ ክርስቲያናቸው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ጥምቀት እንዴት እንደምታከብርና ለተከታዮችዋም ሥርዓተ ጥምቀትን እንዴት እንደምትፈጽም የሰጡትን አስተያየት በዚህ እትም አቅርበናል ።

በመጀመሪያም አባ ሙሴ ገ ጊዮርጊስ የክርስቶስን ጥምቀት (በዓለ ጥምቀትን) እንዴት ታከብሩታላችሁ?

በዓለ ጥምቀትን በማክበር ሥነ ሥርዓት ረገድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መካከል ብዙ ልዩነት የለም ። በገጠር ኢትዮጵያ ያለችው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ወንዝ ወርዳ ድንኳን ተክላ በዓለ ጥምቀትን ታከብራለች በከተማ ያለችው ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ግን የቦታው ሁኔታ ስለሚያመቻት ወንዝ አትወርድም። በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ለበዓሉ አከባበር የሚያስፈልገውን ዝግጅት በማሟላት በዓሉን በሚገባ ታከብራለች ። የአከባበሩም ሥነ ሥርዓት በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውሃ ይዘጋጃል ። ስብሐተ እግዚአብሔር ከተደረሰበት ፤ ጸሎት ከተጸለየበትና ከተባረከ በኋላ በዓሉን ለማክበር በዓውደ ምሕረቱ የተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል የሚተርፈውንም የተጸለየበትን ውሃ ምእመናኑ ይከፋፈሉታል በጸበልነቱ ፈዋሽ ነውና ።



አባ ሙሴ ገ ጊዮርጊስ

የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ምሥራቃዊትና ምዕራባዊት ተብላ ትጠራለች ። የምሥራቅዋ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ትሠራለች በኢትዮጵያም ያለችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባልተለየ ሁኔታ በዓለ ጥምቀትን ታከብራለች ። በኢትዮጵያ የምትገኘው ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ብዙ ግንኙነት ቢኖራትም ትክክለኛው ሥርዓት የምሥራቁ እንደ ሆነ ታምናለች ። በዓለ ጥምቀትንም በቤተ ክርስቲያን የምናከብረው ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ የእኛን ጥምቀት የቀደሰበትን አላማ ለማስታወስ ነው ።

2 ቤተ ክርስቲያናችሁ ለተከታዮችዋ ጥምቀትን መቼና እንዴት ትፈጽማለች ? በወንዶችና ሴቶች ተጠማቂዎችስ ላይ በጥምቀት አፈጻጸም የሥርዓት ልዩነት አለ ወይ ?

በጥምቀተ ክርስትና አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት በወንዶችና በሴቶች ልዩነት የለም የዕድሜ ወሰንም የለም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እንደመጡ ይጠመቃሉ ፤ ሕፃናትም ቢሆኑ ወላጆቻቸው እንደ አመጡአቸው ይጠመቃሉ እንጂ ወንድ ሕፃን በአርባ ሴት በሰማንያ ቀን የሚል ውሳኔ የለም ግን ከአሥራ ሁለት ዓመት በታች ላሉ ተጠማቂዎች ጥምቀት ብቻ እንጂ ቅብዓተ ሜሮንና ሥጋወደሙ አይፈጸምላቸውም ሜሮንና ሥጋወደሙ የሚሰጣቸው ከአሥራ ሁለት ዓመት በኋላ ነው ። ተጠማቂው ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ ከሆነ ግን ሁሉም በአንድ ጊዜ ይፈጸምለታል ።

3ኛ የሌላ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረ የእናንተ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ቢፈልግ እንዴት ትቀበሉታላችሁ ? እንደገና አጥምቃችሁ ነው ? ወይስ በቀደመው ጥምቀቱ ትቀበሉታላችሁ?

በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን የተጠመቀ መሆኑ ከተረጋገጠ ድጋሚ አናጠምቅም ድጋሚ ጥምቀት ክልክል ነው ። በተለይ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተጠመቀ ከሆነ ጥርጥር የለበትም እምነቱም ሆነ ሥርዓቱ [illegible] ነውና ። ግን ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በውሃ የተጠመቀ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል ።

2ኛ ቄስ ኮሊን ባትል በኢትዮጵያ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቄስ

በእንግሊካን ቤተ ክርስቲያን በዓለ ጥምቀት የሚከበረው በወንዝ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ነው አከባበሩም [illegible]

ለተከታዮች[illegible] ጥምቀት [illegible] መው ወላጆች [illegible] ሥርዓተ ሜሮን የምታደርሰውና ሥጋወደሙ የምታቀብለውም ከአሥር ዓመት በኋላ ነው ። ከአሥር ዓመት በላይ የሆነ ሲጠመቅ ግን ሜሮንና ሥጋወደሙም ወዲያውኑ ይፈጸምለታል ። በጥምቀት አፈጻጸም ለወንዶችና ለሴቶች የሥርዓተ ልዩነት የለም ። ግን ለአንዲት ሴት ልጅ ሁለት የክርስትና እናቶች አንድ የክርስትና አባት ፤ ይኖሩአታል በአንጻሩም ለአንድ ወንድ ልጅ ሁለት የክርስትና አባቶች አንዲት የክርስትና እናት እንዲኖሩት ይደረጋል ።



ቄስ ባትል ኮሊን በኢትዮጵያ የአንገሊካን ቤተ ክርስቲያን ካህን

3ኛ የሌላ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረ የአንገሊካን ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ቢፈልግ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ መጠመቁ ከተረጋገጠ ድጋሚ አይጠመቅም ግን አጥማቂው የእግዚአብሔርን አንድነት ሦስትነት የሚያምንና የማያምን መሆኑ በጥብቅ ይመረመራል ። ከጥናቱ በኋላ 1ኛ የአጥማቂው እምነት ትክክል 2ኛ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ የተጠመቀ መሆኑ ከታወቀ በድጋሚ ማጥመቅ ክልክል ነው ምክንያቱም ጥምቀት አንዲት ናትና ።

3ኛ በኢትዮጵያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ፋዘር ኒክታሪዮስ

በየዓመቱ ጥር 6 ቀን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት ምክንያት በማድረግ ጳጳሱ ፤ ቄሱና ምእመናኑ ሁሉ ወደ ባሕር ወይም ወደ ወንዝ ይወርዳሉ ። ቀደም ሲል ግን ልዩ ሥነ ሥርዓት ይደረጋል ። ከባሕሩ (ከወንዙ) ሲደርሱ ዲያቆኑ ይዘምራል ፤ ከአለ ጳጳሱ ከሌለም ቄሱ ወንጌል ያነብባል ከዚያም በኋላ ጳጳሱ ወይም ቄሱ ባሕሩን በመስቀል ሦስት ጊዜ ባርኮ መስቀሉን በባሕሩ ላይ ይጥለዋል ። በዓሉን ለማክበር የተሰበሰቡ ወጣቶች ይዋኛሉ መስቀሉንም ለማውጣት ይሽቀዳደማሉ ፤ በቅድሚያ መስቀሉን የሚይዘው ወጣት ለቄሱ ወይም ለጳጳሱ ይሰጠዋል ። በዓለ ጥምቀት በመላው ግሪክ ብሔራዊ



ፋዘር ኒክታርዮስ በኢትዮጵያ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ቄስ

በዓል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ዝግ ሆነው ይውላሉ በዚያን ጊዜ በባሕሩ ላይ የሚኄዙ መርከቦች ካሉ ደወል ይደውላሉ መዝሙር ይዘምራሉ ። ይህ የጥምቀት በዓል አከባበር የተጀመረው በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ነው የጀመሩትም የጌታ ደቀ መዛሙርት ናቸው ፤ ደቀ መዛሙርት ማስተማር በጀመሩ ጊዜ ብዙ ሰዎች አመኑ ፡ የአመኑትም ሁሉ ወደ ወንዝ እየወረዱ ይጠመቁ ነበር እንደኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ማለት ነው ። ራሱ ክርስቶስም የተጠመቀው በዮርዳኖስ ወንዝ ስለሆነ ይህን በማስታወስ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀትን በዓል በየዓመቱ ወንዝ እየወረደች ታከብራለች ።

ስለ ሕፃናት ጥምቀት የተወሰነ ጊዜ የለም ወላጆች በተመቻቸውና በፈቀዱ ጊዜ እንደ አመጡአቸው ይጠመቃሉ ። ግን አንድ ያልተጠመቀ ሕፃን ቢታመምና ሞት የሚያሰጋው ቢሆን በጊዜውም አጥማቂ ካህን ማግኘት ባይቻል አባቱ ወይም ከምእመናን አንዱ ሕፃኑን ወደ ሰማይ አንሥቶ በመያዝ "አሰግድከ በስመ አብ፣ አሰግደከ በስመ ወልድ፣ አሰግደከ በስመ መንፈስ ቅዱስ" እያለ መስቀለኛ ያሰግደዋል ። የጥምቀት (የክርስትና) ስም ይሰጠዋል ። ይህም የአየር ጥምቀት ይባላል ።

ግን የታመመው ሕፃን በሐኪም ቤት ቢሆን በሐኪም ቤቱም አቅራቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም ምሥጢረ ጥምቀትን የሚፈጽም ካህን ባይኖር ከሕፃኑ ወላጆች ወይም ከሐኪሞች (ክርስቲያኖች) በብርጭቆ ውሃ ወስዶ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይረጨዋል ፤ ስመ ክርስትናም ይሰይመዋል ከዚህ በኋላ ልጁ ከሞት ቢድን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወስድና በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ ሊፈጸም የሚገባው ጸሎት ከተደረሰ በኋላ ቅብዓተ ሜሮንና ቁርባን ይሰጠዋል እንጂ ጥምቀት አይደገምም ። በማለት የሦስቱም አብያተ ክርስቲያናት ካህናት የየቤተ ክርስቲያናቸውን ሥርዓተ ጥምቀት ገልጠዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ክርስቶስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሂዶ በዮሐንስ እጅ መጠመቁን ለማስታወስ በየዓመቱ ጥር 11 ቀን ወደ ወንዝ ፤ ወይም ውሃ ወደሚገኝበት ቦታ እየሄደች በዓለ ጥምቀትን ታከብራለች፤ በሕፃናት ጥምቀት ረገድ ግን ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት የተለየ ሥርዓት አላት ። ይኸውም ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ሴት ልጅ በ80 ቀን እንዲጠመቁ ሥርዓት መሥራትዋ ነው ። ግን ከ40 እና ከ80 ቀን አስቀድሞ ሕፃኑ ቢታመም በሞግዚት ወደ ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ እንዲጠመቅ ሥርዓትዋ ያዝ ያገዛል ። እየተፈጸመም ነው ።

የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያምኑ ሥልጣነ ክህነትን የሚያከብሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጥምቀት የኃጢአት ሥርየትንና የእግዚአብሔር ልጅነትን እንደሚያስጥ ያምናሉ።እንዲሁም ሃይማኖት አንዲት እንደሆነች ጥምቀትም አንዲት መሆንዋን ያስተምራሉ ።

ራደ አስረስ



www.ethiopianorthodox.org

# ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ



ወልደ ነጎድጓድ በመባል ተለይቶ የታወቀው ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጅ የያዕቆብ ወንድም ነው ። ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ዓሣ አጥማጅ ነበር ። ዓሣ ከማጥመድ ሥራውም ጋር የመጥምቁ ዮሐንስን ትምህርት ይከታተል ነበር ። በግልጥ አነጋገር የዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር ለማለት ይቻላል ።

አንድ ቀን ዓሣ በማጥመድ ሥራው ላይ እንዳለ የጌታችን የኢየሱስክርስቶስ ጥሪ ደረሰው ። ወዲያውም ሁሉን ነገር ትቶ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ሆነ ትውፊት እንደሚያስረዳን ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ከአራቱ ወንጌላት አንዱን የመጨረሻውን ወንጌል ከሰባቱ መልእክታት ሦስቱን መልእክታትና መጽሐፈ ራእዩን ጽፎአል ። ዮሐንስ ከሦስቱ ቀራቢዎች ወይም ምሥጢራውያን ደቀ መዛሙርት አንዱ ነው ። እነርሱም ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ ናቸው ። ምሥጢራውያን መባላቸውም ሀ ጌታ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ከሞት ባስነሣ ጊዜ ለ በደብረ ታቦር ምሥጢረ መለኮቱን በገለጠ ጊዜ ሐ በጌቴሴማኒ በጸለየ ጊዜ እነዚህ ሦስቱ ደቀመዛሙርት ብቻ አብረውት ነበሩ ።

ዮሐንስ በግብሩና በጠባዩ በተለየየ ቅጽል ስሞች ይጠራል ። ለምሳሌ ቁጡና ፈጣን ስለነበር ወልደ ነጎድጓድ እንደተባለ በሊቃውንት ይተረጐማል ። በተጨማሪም ነጎድጓድ መደንገፅ እንደ ሆነ ዮሐንስም መደንግፀ መናፍቃን በመሆኑ ወልደ ነጎድጓድ እንደተባለ የተረጐሙ ሊቃውንት አሉ ። (ማር. 9 ፡ 38 - 39 ሉቃ. 9 ፡ 54)

ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ (የጌታ ወዳጅ) በመባል ይጠራል ። እንደዚሁም የፍቅር ሐዋርያ ይባላል ይህ ስያሜ ዮሐንስ ስለ ክርስቲያናዊ ፍቅር በብዛት ከመጻፉ በላይ "እግዚአብሔር ፍቅር" እንደሆነ ደጋግሞ መጻፉን ያመለክታል ።

እርግጥ ፍቁረ እግዚእ" በመባል የሚጠራው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ መሆኑ እስከ አራተኛው ምእት ዓመት ገደማ ድረስ አልታወቀም ነበር ። ምክንያቱም አራተኛው ወንጌል ፍቁረ እግዚእ ወይም ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር ብቻ ይላል እንጂ ስም ለይቶ አይጠራም ። ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም አንዳንዶቹ ፍቁረ እግዚእ የተባለ ማርቆስ የተሰኘው ዮሐንስ እንጂ የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ እንዳይደለ ተናግረዋል ጽፈዋልም ። (አውሳብዮስ የቤ. ክ. ታሪክ 6 ፡ 25)

ኢትዮጵያዊው ሊቅ መልአከ ፀሐይ ተገኝም "ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት ። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው ። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ወደቤቱ ወሰዳት-ዮሐ 19፡26-27)የሚለውን ንባብ ለቅዱስ ማርቆስ ሰጥተው ተርጉመዋል ። ምክንያቱን ሲገልጡ በኢየሩሳሌም ውስጥ የቅዱስ ማርቆስ የእናቱ ቤት ነበር እመቤታችንም ከዕለተ ዐርብ እስከ በዓለ ሃምሳ በቅዱስ ማርቆስእናት በማርያም ቤት ነበረች ለዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድግን በገሊላ እንጂ በኢየሩሳሌም ቤት አልነበረውም ስለዚህ "ወደቤቱ የወሰዳት ደቀመዝሙር ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ጽፈዋል (የሐዋ.1 ፡ 12-14 12 ፡ 12 )

በኋላ ግን በአምስተኛው ምእትዓመት ገደማ ልክ ዛሬ እንደሚታመነው ፍቁረ እግዚእ ወይም ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር የተባለ ዮሐንስ (የዘብዴዎስ ልጅ) ወልደ ነጎድጓድ እንደሆነ ተረጋገጠ ከዚህም የተነሣ በመጨረሻ ራት ጊዜ በጌታ አጠገብ ተቀምጦ የነበረው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ ነው እነኋት እናትህ እነሆ ልጅሽ ተብሎ የተነገረለት ደቀ መዝሙርም ዮሐንስ ነው ።

በትንሣኤ ሌሊትም ከጴጥሮስ ጋር ወደ ጌታ መቃብር የሮጠው ደቀመዝሙር ይኸው ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ እንደሆኑ ቤ. ክርስቲያን አረጋግጣ ተቀበለች ከዕርገት በኋላ ዮሐንስ በኢየሩሳሌም ከጴጥሮስ ጋር ታላላቅ ሥራዎችን ሠርቷል በሐዋርያት ሥራ 3 ፡ 1 እና 11 ላይ እንደተገለጠ ሽባውን ሰው በጌታ ስም አድኖአል ። በሕዝብና በሊቃነ ካህናት ፊት ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣ ክርስቶስ ከጴጥሮስ ጋር በግልጥ መስክሮአል (የሐዋ.4 ፡ 1 - 21) የሰማርያ ሰዎች አምነው ከተጠመቁ በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ቅዱስ ዮሐንስ ከጴጥሮስ ጋር ጸለየላቸው (የሐዋ.8 ፡ 14) ለመጀመሪያ ጊዜ በኢየሩሳሌም በተደረገው ሲኖዶስ ዮሐንስ ተገኝቷል የሐዋ. 15 ።

ዮሐንስ በመጨረሻ ጊዜ ወደ ትንሹ እስያ ሄዶ በኤፌሶን ከተማ ይኖር ነበር ኤፌሶን በአሁኑ ጊዜ በቱርክ ውስጥ ይገኛል የክርስትና ምልክቱ ግን ጠፍቷል ። ዮሐንስ በኤፌሶን ሳለ ዶምጥያን የተባለው መሪ በፍጥሞ ደሴት አጋዘው በዚያም ሳለ ራእዩን ጻፈ እንደገናም በአርባ ዘመን ወደ ኤፌሶን ተመልሶ ወንጌሉንና ሦስቱን መልእክታት ጻፈ ።

ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ከሌሎች ሐዋርያት ሁሉ በፊት እንደተጠራ ከሐዋርያት ሁሉ በኋላ የሞተ መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ። ነገር ግን ዮሐንስ እንደ አልሞተና እስካሁን ድረስ ከገጸ ሞት ተሰውሮ እንደሚኖር የሚተርኩ አንዳንድ ሊቃውንት አሉ ። እነርሱ መነሻ ያደረጉት በአራተኛው ወንጌል በምዕራፍ 21 ፡ 21 - 24 በስም ስለ አልተገለጠው ደቀመዝሙር የተጻፈውን ዐረፍተ ነገር ነው ። ነገር ግን ጥቅሱ "ጌታችን ኢየሱስ እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ አለ እንጂ አይሞትም" አላለም ።

ስለዚህ ብዙዎቹ የቤ ክ ታሪክ ጸሐፊዎች "ዮሐንስ አይሞትም" የሚለው ዜና በኋላ እንደተጨመረ ይናገራሉ ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ስለዚህ አስተያየታቸውን ሲሰጡ ከዮሐንስ ወንጌል 21ኛውን ምዕራፍ አብሮ ኮሮስ የተባለው የዮሐንስ ደቀ መዝሙር እንደጻፈው ይተርካሉ ። በዚህ አንጻር "ዮሐንስ አልሞተም" የሚለው ዜና የወጣ ከአብሮኮሮስ ነው ። ለዚህም ሀሳብ መሠረቱ "የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ" ማቴ.16 ፡ 28) የሚለው ጥቅስ ነው ለዚህም የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል ። ለምሳሌ በመንግሥቱ ሲመጣ ማለት በደብረ ታቦር ምሥጢረ መንግሥቱን ሲገልጥ እስኪያዩ ድረስ የማይሞቱ አሉ ማለት ነው ብለው የሚተረጉሙ አሉ ። ከዚህም ሌላ በዕለተ ትንሣኤ ተነሥቶ እስኪያዩት ድረስ ማለት እንደሆነ የሚመለከቱ አሉ ። ሌሎች ደግሞ በትክክል በዕለተ ምጽአት በግርማ መንግሥት ሲመጣ እስኪያየው ድረስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ሞትን አይቀምስም ማለት እንደ ሆነ ይተረጉማሉ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ዮሐንስ አልሞተም በሚለው ሀሳብ አይስማሙም ። ግን በ90 ዓመት ዕድሜው እንደ ሞተ ያምናሉ ።

ያም ሆነ ይህ ዮሐንስ ዛሬ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ሕያው ነው በሥራው ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖራል ምሥጢረ መለኮትንና ምሥጢረ ሥጋዌን

አምልቶና አጉልቶ የጻፈ ታላቅ ሐዋርያ ነውና ከዚህም የተነሣ "ዘንስር ዮሐንስ" ይባላል ። በቤተ ክርስቲያን የሥዕል ዓለም ንስር በአጠገቡ እንዳለ ሆኖ ይሣላል ። ይህም መጥቆና ረቅቆ የሚያስብ ልዑለ ስብከት መሆኑን ያመለክታል ። ዮሐንስ በሽምግልናው ጊዜ ሁሉ የሚያስተምረው ትምህርት "ልጆቼ እርስበርሳችሁ ተፋቀሩ" የሚለው ቃል ነበር ደቀ መዛሙርቱም አባታችን ለምን ሁል ጊዜ አንድ ዓይነት ትምህርት ታስተምራለህ? ሲሉት "ልጆቼ ይህ የጌታ ትእዛዝ ነው" በማለት ይመልስላቸው ነበር ።

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታላቅና ተወዳጅ ሐዋርያ በየዓመቱ ጥር 4 ቀን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ። በዚሁ ዕለት በስሙ በታነፁ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ያስተማረው ትምህርት ያደረገው ምግባርና ትሩፋት ይታወሳል ። ጥር አራት ቀን ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየበት መሆኑን ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ብዙዎቹ ያምናሉ ።**

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# የሲዳማ ብሔረሰብ ባህል

በዚህ ዐምድ ሥር ባለፈው እትም በ ሲዳሞ ክፍለ ሀገር በስድስቱም አውራ ጃዎች ውስጥ ተሰበጣጥረው የሚኖሩ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች መኖራቸው ተጠ ቅሶ ነበር እነዚህም የጌዴኦ የሲዳማ የአ ማሮ (ኮይራ) የጉጂና ቦረና ፣ የቡርጂ የ መርሐን የሎሳን ፣ ገረ መሮና ፣ ዲጐዳዩ የተባሉትን ዘርዝረን ነበር ። በዚህ እት ም ደግሞ ስለሲዳማ ብሔረሰብ ባህል እናወሳችኋለን ።

የሲዳማ ብሔረሰብ በሲዳማና በጐረ ቤት አውራጃዎች ጭምር ይኖራል።ብ ሔረሰቡ በብዛት የሚኖርበት የሲዳማ አውራጃ እንደተቀሩት የክፍለ ሀገሩ አ ራጃዎች ሁሉ በልምላሜ የታደለ ነው። በዚህ ሥፍራ ከሚመረቱት ልዩ ልዩ አ ዝርእቶች ሌላ ይህ አውራጃ በቡና ሰብ ል እውቅ ነው ።

## ቤተሰብና ኑሮ

የሲዳማ ብሔረሰብ እንደጐረቤቱ እ ንደ ጌዴኦ ብሔረሰብ ሁሉ ቤተዘመዱ ተቀራርቦ የመኖር ባህል አለው በዚህ ሁኔታ ቤተዘመዱ በክፉውም በደጉም ይረዳዳል ። አብሮ ይሠራል አብሮ ይበ ላል በዓላትን አብሮ ያከብራል ። ብሔ ረሰቡ በሥራ ወቅት የመተጋገዝ ባህል ስላለው የሩቁም የቅርቡም በደቦ (በደ ቦ) ወጥቶ ምንጣሮ ይመነጥራል ። በሬ ጠምዶ ያርሳል የብሔረሰቡ አባላት ቤ ት ለቸገረው በአንድ ጀንበር መጥተው አዋቅረው ያስረክቡታል ። ይህን የመ ሳሰለው የደቦ ወይም የጂጌ ሥራዎች በ ሚከናወኑበት ወቅት እርዳታ ጠያቂው ሰው ከብት አርዶ ከእንሰት ከሚዘጋጅ ምግብ ጋር ጠላ አድርጐ ያቀርባል ።ደ ቦኞቹ በሚሠሩበትም ሆነ በሚጋበዙበ ት ጊዜ ያዜማሉ ይዘፍናሉ ።

### በዓላትና ኪነት

የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት በልዩ ሥ ነ ሥርዓት ከሚያከብሩዋቸው ባህላዊ በዓላት አንዱ ፊቼ የተባለው ነው ። ይህ በዓል በዓመት አንድ ጊዜ ይከበራል ። ቤተሰቦች በሽማግሌ አባቶቻቸው ቤት ተሰብስበው የደገሱትን በአንድነት ሁ ነው በልተው ጠጥተው ይደሰታሉ ።መ ላው ህብረተሰብም ባንድነት ሁኖ ይህ ን በዓል ያከብራል ።

የሲዳማ ብሔረሰብ ጐረምሶችና ኮረ ዶች ኪነትን ይወዳሉ ። በየበዓላቱና በ ሠርግ ወቅቶች ተጠራርተው ይወጡና ጐረምሶቹ በአንድ ረድፍ ልጃገረዶቹ በሌላው ትይዩ ሁነው አውራጅ በሚያ ቀነቅነው ሙዚቃ እየተመሩ ዳንኪራ ይ መታሉ ። ጐረምሶቹ ረጂም እጀጠባብ ከሱሪ ጋር ለብሰው በላዩ ላይ ጋቢ ደ ረብ ያደርጋሉ ። ኮረዶች ፀጉራቸውን ሹ ሩባ ተሠርተው ከታች ዳሩን በዛጐል ያ ጌጡታል ። ከውስጥ ቀሚስ አጥልቀው ከላዩ ላይ ከቆዳ የተሠራ የተጌጠ ሙሉ ካባ ይደርባሉ ። ጀግኖቹ ዝንጉርጉር የባ ህል ልብሳቸውን ለብሰው በላዩ ላይ የአ ንበሳ የነብር ወይም የጉሬዛ ለምድ ደር በው ሰፊ ጋሻ ከረጅም ጦር ጋር ይዘው በኅብረት እየሸለሉ ይፎክራሉ ። ይህ የ ኅብረት ሽለላና ፉከራ በሩቁ ጠላትን የ ሚያርበደብድ ይመስላል ።

## ጋብቻ

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራ ዎች በሚኖሩ ብሔረሰቦች ዘንድ እንደ ሚታየው ሁሉ በሲዳማ ብሔረሰብ ዘን ድም ልዩ ልዩ የተለምዶ የጋብቻ አፈጻ ጸም አለ ።

-አንደኛው የጋብቻ ዓይነት በአባትና በእናት ታውቆ በሁለቱም ወጣቶች ወ ላጆች ስምምነት የሚደረግ ጋብቻ ነው በዚህ ወቅት የልጁ አባት ወደልጂቱ ቤ ት ሂዶ ልጃቸውን ለልጁ እንዲሰጡት ይጠይቃል ። የልጂቱም ወላጆች የልጁ ን ጠባይና ሁኔታ ካጠኑና ካስጠኑ በኋላ ቀጠሮ ተደርጐ በሠርግ ትዳራለች ። ለ ቀጠሮ ተደርጐ በሠርግ ትዳራለች ። ለ ጋብቻ ከሚደረጉ ዝግጅቶች አንደኛው ልጃገረድን ማስገረዝና ለሁለት ወር መ ጠበቅ ነው ። በጋብቻ ዕለት ሙሽራው ወደ ሙሽሪት ቤት ታጅቦ ይሄድና ከተ በላና ከተጠጣ በኋላ በመጣበት ሁኔታ ታጅቦ ሙሽሪትን ከሚዜዎቹ ጋር ይዞ ይመለሳል ።

ሁለተኛው የጋብቻ ዓይነት ደግሞ ሙሽራው ወደ ልጂቱ ቤት ታጅቦ ከሄ ደ በኋላ እርሱ ካጃቢዎቹ ጋር ራቅ ብሎ ይቆይና ሚዜዎቹ ወደ ልጂቱ ቤት ይላ ካሉ ። እነርሱም ከደጅ ሲደርሱ በር ላይ ይቆማሉ ። መምጣታቸው እንደታወቀ እናት ልጅዋን ቅቤ ቀብታና አስጊጣ ለ አባትዋ ትሰጣለች አባትዋም እንግዶ ቹን ወደ ቤት አስገብቶ "የልጁ ጥርስ እንዳይሰበር ዓይንዋ እንዳይፈስ ጀሮዋ ም እንዳይደነቁር" በጥንቃቄ ጠብቋት በማለት አስጠንቅቆ ከምክር ጋር ይሸ ኛቸዋል ። ሙሽራውም ልጂቱን ይረከ ብና ታጅቦ ወደ ቤቱ ያመራል ። በበነጋ ታውም ልጂቱ ተገርዛ ለሁለት ወራት መልካም ምግብ እየተመገበች ትቆያለ ች ።

ሦስተኛው ጋብቻ ደግሞ ጐረምሳው ደስ የምትለውን ኮረዳ ሲያጋጥመው እ ንደሚወዳት ፊትለፊት ወይም በሰው በኩል ይገልጽላትና ለጋብቻ ይጠይቃ ታል ። እሺ ካለች ተያይዘው ይገባሉ ። እርስዋም አብራው ስትሄድ ወላጆችዋ እንዳይደነግጡ የጨርቅ ቋጠሮ ምልክ ት በምኝታዋ ራስጌ ትታ ትሄዳለች ም ልክቱም ማግባትዋን የተረጉምላቸዋል ከዚያም ልጁ ወደወላጆችዋ አማላጅ ል ኮ ካሣ ከከፈለ በኋላ ይታረቃል ።

አራተኛው ደግሞ አደዋና ማለትም ወዶ-ገብ ጋብቻ ነው ። ይህ ልጂቱ ወን ዱን በመልኩ ቀናነት ወይም በሀብት ብ ዛት ስትማረክ ወዳ ትገባለች ። ይህ እን ግዲህ አግቢዋ ዘንግ ትይዝና ወደ ሰው ዬው ወላጅ ቤት ሄዳ እናቱ መኖራቸው ን ካረጋገጠች በኋላ እቤት ውስጥዘውብ ላ ገብታ ዘንጉን ወደጋጣ ትወረውረዋ ለች ። የልጁ እናትም ከተቀበልዋት ወ ደውስጥ ያስገብዋታል ። ዝግጅት ተደ ርጐ ከተገረዘች በኋላ ጋብቻው ይፈጸማ ል ። ከዚያም ጥሎሽዋ ለወላጅዋ ይላካ ል ። ዳሩ ግን ልጂቱ ከልጁ ጋር የሥጋ ዝምድና ያላት መሆኑ ከታወቀ ቅቤ ተ ቀብታ ወደ ወላጆችዋ እንድትመለስ ይ ደረጋል ።

ተከታዩን በገጽ ፲፪ ይመልከቱ



# ትምህርተ ግዕዝ

# የግእዝ ትምህርት

## ትምህርት 3

አገናዛቢ ዝርዝር/አጸፋ ተውላጠ ስም አንድ ነገር የማን እንደሆነ ለማወቅ የ ምንጠቀምባቸው ፊደላት የሚከተሉት ናቸው ።

| ነጠላ | ብዙ |
|---|---|
| የ | ነ |
| ከ | ክሙ |
| ኪ | ክን |
| ካዕብ | ሳብዕ እና ሙ |
| ራብዕ | ሳብዕ እና ን |

ምሳሌ « ቤት »

| ነጠላ | አማርኛ |
|---|---|
| ቤትየ | ቤቴ |
| ቤትከ | ቤትህ |
| ቤትኪ | ቤትሽ |
| ቤቱ | ቤቱ |
| ቤታ | ቤትዋ |

| ብዙ | አማርኛ |
|---|---|
| ቤትነ | ቤታችን |
| ቤትክሙ/ ተባ / | ቤታችሁ |
| ቤትክን / አን / | ቤታችሁ |
| ቤቶሙ/ ተባ / | ቤታቸው |
| ቤቶን / አን / | ቤታቸው |

ከዚህ በላይ ባጠናነው የእርባታ ሕግ ዐረፍተ ነገር ለመሥራት እንድንችል የሚከተሉትን ቃላት እንመልከት ።

| | |
|---|---|
| አይቴ | ወዴት |
| ዝየ | እዚህ |
| ሀየ | እዚያ |
| ከሀ | ወዲያ |
| ጥቃ | አጠገብ |
| ፍኖት | መንገድ |

## ዐረፍተ ነገር

### ተስእሎ ( ጥያቄ )

ነጠላ

| | |
|---|---|
| አይቴ ውእቱ ቤትከ ? | ቤትህ ወዴት ነው ? |
| አይቴ ውእቱ ቤትኪ ? | ቤትሽ ወዴት ነው ? |
| አይቴ ውእቱ ቤቱ | ቤቱ ወዴት ነው ? |
| አይቴ ውእቱ ቤታ ? | ቤትዋ ወዴት ነው ? |
| ዝየ ውእቱ ቤትየ | ቤቴ እዚህ ነው |
| ሀየ ውእቱ ቤትየ | ቤቴ እዚያ ነው |
| ከሀ ውእቱ ቤቱ | ቤቱ ወዲያ ነው |
| ጥቃ ቤተ ትምህርት ውእቱ ቤታ | ቤትዋ ትምህርት ቤቱ አጠገብ ነው |

ብዙ

| | |
|---|---|
| አይቴ ውእቱ ቤትክሙ ( ተባ ) | ቤታችሁ ወዴት ነው ? |
| አይቴ ውእቱ ቤትክን ( አን ) | ቤታችሁ ወዴት ነው ? |
| አይቴ ውእቱ ቤቶሙ ( ተባ ) | ቤታቸው ወዴት ነው ? |
| አይቴ ውእቱ ቤቶን ( አን ) | ቤታቸው ወዴት ነው ? |
| ዝየ ውእቱ ቤትነ | ቤታችን እዚህ ነው |
| ሀየ ውእቱ ቤትነ | ቤታችን እዚያ ነው |
| ጥቃ ፍኖት ውእቱ ቤትነ | ቤታችን መንገድ አጠገብ ነው |
| ከሀ ውእቱ ቤትነ | ቤታችን ወዲያ ነው ። |

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፭ የዞረ

"አነ ወዝናም
በኩሉ ነገር
እንዘ ንጹሐን ንሕነ
አሮን ለበዊአ ቤቱ
በከንቱ ከልአነ..."

እኔና ዝናም በሁሉ ነገር ንጹሐን ስን ሆን አሮን ወደቤቱ እንዳንገባ በከንቱ ከለከለን ። የቅኔው ዋና ዓላማ የአለቃ ለማን ከአቡነ አሮን ደብር ወጥተው መቅረትንና ዝናም በቤተ ክርስቲያኑ የጣራ ቀዳዳ አለመግባቱን ለማነፃፀር ነው ። አለቃ ለማ ተአምራታዊት ወደ ሆነችው ወደ ትውልድ ቦታቸው ለመ መለስ ምኞት ሲኖራቸው በቅኔያቸው ትንቢት መሠረት ወደሀገራቸው ሳይ ገቡ በአዲስ አበባ ዐርፈዋል ።

እንግዲህ ጠያቂው መዝገቡ ገለቱ በሰሜን ኢትዮጵያ ስለሚገኘው የአቡነ አሮን ተአምራዊ ቤተ ክርስቲያን አድ ራሽ እንዲሁም ጣራው ዘጠኝ ስኩዌር ሜትር ክፍት ሲሆን ዝናም ስላለማፍ ሰሱ በመጠኑ በተገለጠው መሠረት እንደተረዱ አዘጋጅው ተስፋ ያደርጋል።



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ



አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ ከአባታቸው ከአቶ ተክለ ማርያም ዲነግዴና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተ ሚካኤል ወልደ ኢየሱስ በ1876 ዓ.ም. በሸዋ ክፍለ ሀገር በይፋትና ጥሙጋ አውራጃ በማፉድ ወረዳ በጃልዬ አምባ ሚካኤል ሰበካ ተወለዱ ።

በተወለዱ በ8 ዓመት ዕድሜያቸው አጐታቸው ቀኝ አዝማች አሻግሬ ወልደ ኢየሱስ ለትምህርት ወደ ደብረ ብርሃን ከተማ ወስደዋቸው አለቃ ገብረ ሚካኤል ከሚባሉት መምህር ቅኔ ከአለቃ ሀብተ ገብርኤል ጸዋትወ ዜማ አጠናቀው ተምረዋል ።

በ1892 ዓ.ም. በመናገሻ አውራጃ ሩፋ በተባለው ደብር እንዲሁም በሰላሌ አውራጃ አራተ ማርያም የቅኔ ትምህርታቸውን ካስፉፉ በኋላ ወደ ደብረ ብርሃን ከተማ ተመልሰው አቋቋምና ዝማሬ መዋሥዕት በሚገባ ተምረዋል ።

ከዚህ በኋላ በ1898 ዓ.ም. ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር ተሻግረው በወረ ሂመኑ አውራጃ ተንታ ሚካኤል በተባለው ታላቅ ደብር ከአለቃ አስካል የሰለልኩላ ቅዳሴ በሚገባ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

ከዚያም ወደ ቤተልሔም ወርደው ከሊቀ ካህናት መርሻ ድጓ አስመስክረዋል ። ቀጥሎም በዙር አባ ከአለቃ ቀለመ ወርቅ ዝማሬና መዋሥዕት አስመስክረው በመምህርነት ተመርቀዋል።

የጸዋትወ ዜማና የአቋቋም ትምህርታቸውን በመቀጠል ጐንደር በአታ ከመሪጌታ ላቀው ግምጃ ቤት ማርያም ከመሪጌታ ገብረ ዮሐንስ እንዲሁም የጸዋትወ ዜማ ይትበሃልና አገባብ ከመሪጌታ ሣህሌ ወልደ ተክሌ በሚገባ አጠናቀው ተምረው ለመምህርነት ከበቁ በኋላ በደንቢያ በገራገራ ቅዳሴ ጾመ ድጓ ምዕራፍ አቋቋም ዝማሬና መዋሥዕት ሲያስተምሩ ቆይተው በ1912 ዓ.ም. ወደ ትውልድ ሀገራቸው በመመለስ ጃልዬ አምባ ሚካኤል እናታቸው ዘንድ እንደ ተቀመጡ በዚያው ዓመት ታቦር ማርያም ወ ሮ ጌጤ ኃይለ ማርያምን በሕግ አግብተው ትዳራቸውን መሥርተው የማስተማር ሥራቸውን ቀጠሉ ።

በ1913 ዓ.ም. ለዳግማዊ አፄ ምኒልክ ፺ ዓመት ፍታት ተጠርተው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በንግሥት ዘውዲቱ ፈቃድ በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት በመምህርነት ተቀጥረው በማስተማር ብዙዎች ደቀመዛሙርትን በትምህርት ወልደዋል ።

በማስተማር ሥራቸውና በጠባያቸው እጅግ የተመሰገኑ በመሆናቸው ከንግሥት ዘውዲቱ 5 ጊዜ ልዩ ልዩ ሽልማት አግኝተዋል ። በማስተማር ሥራቸው ላይ በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የወለሉ ሚካኤል ደብር ዕልቅና ተሰጥቷቸው ከ1915 ዓ.ም. እስከ 1927 ዓ.ም. መጨረሻ አስተዳድረዋል ።

በዚሁ መካከል በ1922 ዓ.ም. ከአቡነ ሳዊሮስ የቅስና ማዕረገ ክህነት ተቀብለዋል ።

በ1928 ዓ.ም. በመስከረም ወር መንዝና ግሼ አውራጃ የሚገኘው ታቦር ማርያም ደብር ዕልቅና በመንግሥት ፈቃድ ተሰጥቷቸው እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ ሲያስተዳድሩና በዚሁ ቦታ ሲያስተምሩ ኑረዋል ።

በማስተማር በኩል ያላቸው የጉባኤ ያቸው ስፋት የተማሪዎቻቸው ብዛት የታወቀ ስለነበር ዝናቸውን በመስማት ከልዩ ልዩ ክፍላተ አህጉር ይጐርፉ የነበሩትን ደቀ መዛሙርት በማስተማር መምህራንንና ከፍተኞች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አስገኝተዋል ።

አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ ከዚሁ ሁሉ

ተከታዩ ወደ ገፅ ፲፭ ዞሯል



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## የሥነ ጥበብ ኤስቴቲክስ ልዩ ልዩ ክፍሎች

ቁጥር . 2 ፦ የሰብአዊ ርኅራኄን ስሜት የሚፈጥር ትርኢት

ከራሳችን ቁጥጥር በላይ የሚሆኑ አንዳንድ ግዙፉን ድርጊቶችና ትርኢቶች የመኖራቸውን ያህል ከእኛ ኃይልና ሥልጣን ሥር የሆኑ ሌሎች ታናናሽ ነገሮችም በአካባቢያችን ይገኛሉ እነርሱንም ስናይ የርኅራኄ ስሜት ያድርብናል ።

ለምሳሌ ፦ ሌላው ቀርቶ የአህያ ውርንጭላ ወይም የውሻ ቡችላ እንዲሁም የበግና የፍየል ግልገሎች የላም እንቦሳ የመሳሰሉት እንስሳት ሲቦርቁና ሲፈነጩ ፤ ወይም ሕፃናት ሲፈነድቁና ድንኩል ድንኩል ሲሉ እንደርግቦች ያሉ አዕዋፍና ሌሎችም ልዩ ልዩ ኅብረ መልክዕ ያላቸውን እንስሳት አራዊትና አዕዋፍ ስንመለከት ወይም ለምለም ዕፅዋትንና የፈኩ አበቦችን ስናይ እጅግ የሚያስፈሩና የሚያሳዝኑ፣ የሚያሳሱም ስለሆነ እንድንጠነቀቅላቸው የሚጋብዝ ማራኪ ትርኢት አላቸው። ይህም ትርኢት ስሜታችንን በመነቅነቅ ለምንወዳቸውና ለምናፈቅራቸው ነገሮች ሁሉ በመራራት የሚቻለንን ሁሉ በማድረግ እንድንጠነቀቅላቸው ያሳስበናል ። ስለዚህም በስነ ጽሑፍ ፣ በሥዕልና በቅርፃ ቅርፅ ሥራ ሁሉ ሐሳቦችን ለመግለጥ እንሞክራለን ማለት ነው ።

ቁጥር 3 ፦ ኮሜዲ

ኮሜዲ ቁም ነገርን በባልትና በጭዋታ መልክ ማቅረብ የሚያስችል የደስታ ስሜት መቅረጫና የትርኢት ማንፀባረቂያ ነው ። በመጀመሪያ ይዘቱ በመጠኑም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ አሳዛኝና አደገኛም መስለው ከሚታዩ አስገራሚ ትርኢቶች ጋር አስደሳችና አስደናቂ ነገሮች ተሰባጥረው በውድድር መልክ የሚታዩበት ሲሆን በመጨረሻ ላይ ግን በትርኢቱ ውስጥ የምንደሰትበትና ድጋፍ የምንሰጠው ክፍል የበላይነትን አግኝቶ በድል አድራጊነት አሸናፊ ሆኖ በሚወጣበት ጊዜ ሐዘናችን ስሜታችን ወደ ደስታ የሚለወጥበት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር የድርሰት ማመንጫ ኃይል ነው ። እርሱም በልዩ ልዩ ዓይነት ጭዋታና ፣ ኩምክናን በተመላ አስደሳችና አስቂኝ የባልት ንግግርና ትርኢት ብዙ ቁም ነገሮችን በመማር የመንፈስ እርካታን የምናገኝበት ብሩህ ድርስት ማንፀባረቂያ ነው ።

ቁጥር 4 ፦ ትራጀዲ

ትራጀዲ የተውኔ ቃል ትርጉም ገድል ማለት ይሆናል ይኸውም የአሳዛኝና አደገኛ ሁኔታዎች መከሰቻ ነው ። እርሱም ብዙውን ጊዜ በሰው ዘር ላይ የደረሰ ወይም ሊደርስ ይችላል ተብሎ የማይጠበቅ ከባድ የሕይወት መቅሠፍትና የኑሮ ፈተና ወይም የሞት አደጋ ምንም ዓይነት በደል ባልሠሩ ሰዎች ላይ የሚያንገዋብብበትን ስሜት የሚፈጥር አስገራሚ ድራማ ይወልዳል።ይህ ዓይነቱ ከባድ ድርጊት የተፈጸመበትን ሰው ታሪክ ወይም ገድል ስንመለከትና ስንሰማ ወይም በፊልም ተቀርጾ ስናየው ወይም በትያትር መልክ ሲቀርብልንና በቅኔም ይሁን በግጥም ወይም በስድ ንባብ ተደርሶ ስናነበው በመጀመሪያ አልፎ አልፎ የሚያሳስቁ አንዳንድ ነገሮች ቢቀላቀሉበትም እንኳ እያሳሳቀ ቀስ በቀስ የትርኢቱን ግርማ መልክ በመለወጥ እመጨረሻ ላይ እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ወይም አሸባሪ ሆኖ ከሚዘገንንና ከሚሰቀጥጥ ሁኔታ ጋር በማጋፈጥ ተመልካቾችን ዓውድ ጥሎ የሚያልፍ ትርኢት ይሆናል ።

ትራጀዲ ምን ጊዜም ቢሆን የሰውን መንፈስ የሚያሸብር ሁኔታን በመፍጠር ደፋር የሆኑ የአንዳንድ ቆራጥ ጀግኖችን የሕይወት ታሪክ በመውሰድ ወይም በልብ ወለድ የፈጠራ ድርሰት ከሞት ወደ ሕይወት ከሕይወትም ወደ ሞት እየመላለሰ ጻዕርና መከራ በማብዛት የተመልካችን የአንባቢዎችን የተርጓሚዎችን ወይም የአድማጮችን ሆድ እያባባ ፈተናን ሁሉ የሚያለማምድና አስፈላጊ በሆነም ጊዜ የሞትን ፅዋ እንኳ እስከመጨለጥ የሚያደርስ ባጠቃላይ አገላለጥ ሞትን የሚያስንቅና ጭንቀትን ሁሉ በማስረሳት የጀግንነትና የድፍረትን ወኔ የሚያጐለምስ በመሆኑ ፈሪዎች ይጠሉታል ቆራጥ ሐሞት ያላቸው ልበ ሙሉዎችና ደፋሮች ግን ይወዱታል ።

ለማናቸውም የተቀደሰ ዓላማና ተግባር ብርታትን ድፍረትን የአልደፈር ባይነትን ጠባይ በሰዎች አእምሮ ከደማቸው ጋር በማዋሃድ ሞትን ሕይወት ፤ ሕይወትንም ሞት አድርገው እንደተመለከቱት አድርጎ በማቅረብ ወኔን የሚቀሰቅስ በመሆኑ ከኮሚዲ ይበልጥ ይመረጣል ይወደዳል ።

ትራጀዲ፦ የትንሽነትንና የደካማነትን ባሕርይ እንደቆብ አውልቆ ለመጣል የሚያስችል የአሸናፊነትን ግርማ የሚያለብስና ክብርን የሚያጐናጽፍ ትምህርት አለው ። በትንሽነትና በደካማነት አንፃር ብርቱነትና ኃያልነት መኖሩን ያስገነዝባል። እኔነትንም በማሳወቅ ወደፊጽም የንፅሕና ኑሮ ይስባል ። ተራ የሆነውን ሰው እንኳ ቀድሞ ከነበረበት የዝቅተኛነት መንፈስ መንጥቆ አውጥቶ ታላቅ ወኔ ወደሚታይበት ከፍተኛ ደረጃ ያደርሰዋል ።

ትራጀዲ በሕይወትና በሞት መካከል ያለውን የዘወትር የኑሮ ትግል የሚያመለክት በመሆኑ ባጠቃላይ ዕረፍትን ሳይሆን ሥራና ድካም የበዛበትን እንቅስቃሴ የሚያሳይ የተነቃናቂ ኃይል ትርኢት ነው ። ይህንም አንቀሳቃሽ የትራጀዲ ትርኢት የተለማመዱት ሕዝቦች ከመንፈሳቸው ከፍተኛነት የተነሳ ምንም ዓይነት ኃይል ሳይበግራቸውና ማንም ሳይደፍራቸው በልበ ሙሉነትና በኩ



www.ethiopianorthodox.org

ሩነት ተከብረው መኖርን ይመርጣሉ ። የሀገራቸውን ዳር ድንበር አስከብረው ነፃነታቸውን እንደተጐናፀፉ ለመኖር የሚያስችላቸውን መሥዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል እያመኑቱም በሰላም ጊዜም ወዳጅነታቸውና ታማኝነታቸው ከብረት የጠነከረ ነው ። በነርሱ ዘንድ ፍርሃትና ወላዋይነት ፣ ዝርክርክነትና ግብዝነት አስመሳይነትና አጉል ጀብደኝነት ቦታ የላቸውም ።

ከዚህም የተነሳ ክርስቲያን ደራሲ በተለይ ከኮሜዲ ይልቅ ትራጀዲ የሆነ ታሪክ ያለው ጽሑፍ ማቅረብ በይበልጥ የሚፈልግበት ምክንያት አለው ።ይኸውም በሃይማኖት ጽናት ረገድ ሰማዕታትን ወይም ጻድቃንን ወደ ገዳም ሲመራቸው የኖረ ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል ። ዓለማዊ ፍላጎትን አሸቀንጥረው ጥለው ሞትን ንቀው እሳቱን ስለቱን ግርፋትንና ስቅላትን ታግሰው ከአራዊት ጋር በመታገል ረኀብን፡ ስደትን ከምንም ሳይቆጥሩ ግርማ ሌሊትን ፣ ድምፀ አራዊትን ሳይፈሩ ዳዋ ጥሰው ደንጋይ ተንተርሰው ጤዛ ልሰው ችግርን ሁሉ ችለው ተወዳዳሪ የማይገኝለት ገድል ትሩፋት በመፈጸም የገጠማቸውን ፈተና ሁሉ በድል አድራጊነትና በአሸናፊነት ሊወጡት ያስቻላቸው የመንፈስ ጥንካሬ ነው የዚህ ውጤት በሥነ ጽሑፍ ሲገለጥ ትራጀዲ ወይም ገድል ይባላል ።

የዚህም ሃይማኖታዊ ትራጀዲ ገድል አስፈጻሚው ኃይል የእግዚአብሔር መንፈስ ነው ። ይህም ሃይማኖታዊ የሆነ ገድል ወይም የትራጀዲ ድርጊት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደውሃ ፈሳሽ አይደለም አስቀድሞ ከነቢያት እንደኢሳያስ ያሉት በመጋዝ በመተርተር እንደነ ዮሐንስ መጥምቁ ያሉት በሰይፍ በመመተር ወዘተ ቀጥሎም በክርስቶስ ሕማማተ መስቀል አፈጻጸም እጅግ በሚያስፈራ ሁኔታ በታላቅ ግርማ ሲያልፍ ታይቷል ። ከዚህም በመቀጠል የቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስና የነያዕቆብ የሰማዕታትነት አሟሟት የነቅዱስ ጴጥሮስ ስቅለት ፣ የነጳውሎስ ሞትረት ባጠቃላይ ከኔሮን እስከ ዲዮቅልጥኖስ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ በሰማዕትነት ላይ የደረሰው ዕልቂት ሁሉ ራሱን የቻለ ትራጀዲ ነው ። ይህን ለመገንዘብ ስንክሳር እስትጉቡዕ እየተባለ የሚጠራውን የብራና መጽሐፍ መድበል ፣ እንዲሁም የካተኮምቡ ሰማዕት የተሠኙትን መጻሕፍት ማንበብ ይጠቅማል ።

ቄስ መክብብ አጥናው

---

## የሲዳማ ብሔረሰብ..

ከገጽ ፰ የዞረ

አምስተኛው የጋብቻ አይነት ደግሞ በጠለፋ የሚፈጸም ነው ። ይህ የሚሆነው በቀጥታ ልጂቱ ራስዋ ለጋብቻ ተጠይቃ ስትከራበት ወይም ወላጆችዋ ተጠይቀው ሳይፈቅዱ ሲቀሩ አግቢው ወደ ምትገኝበት ሥፍራ ከጓደኞቹ ጋር ሄዶ ያደፍጥና ሲያመቸው ጠልፎ ይዟት ይገባል ። ቤት ከደረሰች በኋላ የግዝረት ሥነ ሥርዓት ቀድሞ ይፈጸምና ያገባታል ። ከዚህ የጋብቻ ሁኔታ ሌላ የውርስ ጋብቻ የተባለም በጊዜው ነበር በብሔረሰቡ ዘንድ የተጋቡ ሰዎች ተሳስበው መኖር የሚጠበቅባቸው ግዴታ ቢሆንም አለመግባባት በልዩ ልዩ ምክንያት ከተፈጠረ መፋታት ይፈቀዳል ።

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው የሴቶቹ የጋብቻ ሥርዓት ከግዝረታቸው ጋር የተያያዘ ድርጊት ነው በአንፃሩ ወንዶችም ይገረዛሉ ። ዓላማው ግን ከሴቶች ግዝረት ሰፋ ያለ ነው ። ለወንዱ ግዝረት ከልጅነት ወደ አዋቂነት ደረጃ የሚሸጋገርበት ሥነሥርዓት ነው ። እዚህ ላይ የክብር ምልክት ነው እንደዚሁም ግዝረት ከእምነት ጋር ተዛምዶ አለው ። ለማግባት መገረዝም አለ ።

እዚህ ላይ የተገረዘው ሰው ከዚያን ቀን ጀምሮ በዬትም ቦታና ጊዜ ከራሱ ጐሣ ውጪ ሌላ ሰው ያረደውን ሥጋ አይበላም ።

ባለፈው ሥርዓት የትምህርት እድል ለሁሉም ክፍት ስላልነበረ ሰፊው ሕዝብ በአጉል ልምድ ታስሮ ዓይነ ህሊናው ታውሮ ከፉውን ከደጉ ሳይለይ ይኖር ነበር አሁን ግን በአገኘው የትምህርት እድል ንቃተ ህሊና እየተረዳ ለብዙ ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ በላዩ ላይ ወድቆበት የቆየውን የማይጠቅም ልምድ እየስወገደ ነው ። በዚህ ትግል ውስጥ ከሚገኙት ብሔረሰቦች መሃል የሲዳማ ብሔረሰብ ይገኝበታል ።



---

# የአልኮሆል መጠጥ ጉጅነት


ተማሪ ነርስ የሽአረግ ሥርጋቄ

በመሠረቱ የአልኮል መጠጥ ኃጢአት አይደለም ወንጀልም አይደለም ። ይሁን እንጂ የኃጢአት ፣ የወንጀል እንዲሁም የጤና መቃወስ ምክንያት መሆኑ አይካድም ። ሰዎች አልኮልን መጠጣት የሚጀምሩት ከሀሳብ ለመዳን ጭንቀታቸውንና ብስጭታቸውን ለመርሳት ከጓደኞቻቸው ጋር ለመገናኘትና ለመጨዋወት እንዲሁም ራሳቸውን ለማዝናናት እንደሆነ ይናገራሉ ።

ነገር ግን የአልኮሆል መጠጥ ለአንድ ግለሰብ በኅብረተሰቡ ውስጥ ሲኖር በጤናው ፣ በኢኮኖሚ እንዲሁም በእምነት አንጻር ሲታይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው ። ከዚህም ውስጥ ታላቁና የመጀመሪያው ችግር ጠጪው በሱስ መጠመዱ ነው ። መጠጡንም ካላገኘ በውስጡ ደስታ አይሰማውም አእምሮውም በትክክል ስለማይታዘዝለት በተሠማራበት የሥራ መስክ አጥጋቢ ውጤት አያሳይም ።

መጠጡን በሚወስድበት ጊዜ እውነተኛና ቋሚ ያልሆነ ደስታ ሊሰማውና ከጭንቀቱም ከሀሳቡም ለተወሰኑ ሰዓት ነጻ ሊሆን ይችላል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በሰውነቱ ውስጥ ያሉ ሕዋሳቶች ስለሚደነዝዙ ተገቢ ሥራቸውን ማከናወን ያዳግታቸዋል ። ሰውየው በሚሄድበትም ጊዜ የሰውነቱን ሚዛን ጠብቆ እንዲሄድ የሚያደርገው የአንጐል ክፍል ስለሚነካ በትክክል መራመድ አይችልም ። ከዚህም የተነሣ ይወድቅና በመፈንከት ከበድ ባለ አደጋ ላይም በመውደቅ ችግር ውስጥ ይገባል። እንደበቱን መቆጣጠርና ስሜቱን መግታት ይሳነዋል ። ማንኛውንም ነገር ባለማሰብና ባለማመዛዘን ይሠራል ማስተዋሉ ከእርሱ ጋር የለምና ። ብዙዎችን ተናግሮ ያስቀይማል ማድረግ የማይገባውንም ሁሉ ያደርጋል በዚህ ሳይወሰን ለዝሙት መንፈስም ዘወትር የተጋለጠ ይሆናል ።

ስለሆነም ኅብረተሰቡ በግለሰቡ ላይ ያለው ግምት በጣም ዝቅተኛና የተዋረደ ነው ። እምነት ሊጣልበትም የሚችል ባለመሆኑ ለቁም ነገር የሚያስበው የለም ።

በኢኮኖሚ አንጻርም ስንመለከተው ለመጠጥ የሚያወጣው ገንዘብ በዚያው ሳቢያ በሚያጋጥመው አደጋ ለሕክምና ከሚያወጣውና ሰክሮ ሲንገዳገድ ወንበዴዎች ከሚዘርፉት ጋር ተደምሮ ጠቅላላ የቤተሰቡን ኑሮ ያዛባል ። ሊወጡት ከማይችሉት እዳ ውስጥም እንዲገቡ ያደርጋቸዋል ። ቀጥሎም በቤቱ ውስጥ በሚፈጠረው ጭቅጭቅና ንትርክ ምክንያት ባልና ሚስት ይፋታሉ ልጆች ይበተናሉ ። የተረፈው ገንዘብም ሆነ ቁሳቁስ ለሚስት ፣ ለልጆችና ለሰውየው ይከፋፈላል ። በዚህም ምክንያት የተወሳሰበና ውጥንቅጡ የበዛ ኑሮ ይሆናል ።

የአልኮሆል መጠጥ በጤና ላይ የሚያመጣው ጠንቅ በሰውነት ውስጥ የሚገኙትን ሕዋሳት በማደንዘዝ ተገቢ ሥራቸውን እንዳያከናውኑ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የጨጓራን መላላጥንና የአንጀት መቁሰልን ያስከትላል ። የደም ባንቧዎች እንዲሰፉ በማድረግ ከፍተኛ የራስ ምታት ያስይዛል ። ሰውየው የምግብ ፍላጐቱ በጣም ዝቅተኛ ይሆናል በዚህም ምክንያት ኃይል ያንሰዋል ክብደቱም ይቀንሳል ለበሽታም የመቋቋሚያ ኃይል ስለማይኖረው የተጋለጠና የተጠቃ ይሆናል ።

የአልኮሆሉ አወሳሰድ መጠን እየጨመረ በሄደ መጠን የአንጐል ሴሎች ስለሚደነዝዙና ስለሚደክሙ ሰውየው አስተሳሰቡ እየቀነሰና እየደከመ ትክክለኛነቱንም እየለቀቀ ይሄዳል ። በጉበት ላይም የሚያስከትለው ችግር ሴሎቹን በመግደል ጠባሳ ይፈጥርና በእንግሊዝኛ ሊቨር ሲሮሲስ በመባል የሚታወቀውን በሽታ ያስከትላል ። እንዲሁም ለዝሙት የተጋለጠ በመሆኑ ምክንያት ሊይዘው የሚችለው የአባለዘር በሽታ ሊታለፍ የማይችል ነው ።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱትን ከተመለከትን በእምነት አንፃርም ያለውን በመጠኑ ለማየት እንሞክራለን ። ክርስቲያኖች የዓለም ብርሃን እንደመሆናቸው መጠን ታላቅ ምሳሌነትና አርአያነት ይጠበቅባቸዋል ። በማንኛውም ነገር በአምላካቸውም ሆነ በኅብረተሰቡ ዘንድ ታማኝ መሆን አለባቸው ከአንደበታቸው የሚወጣው ቃል ሰዎችን የሚያሳዝንና የሚያስቀይም ፣ ራሳቸውንም የሚያስገምትና ፍሬቢሶች የሚያደርግ ሳይሆን የሚያንጽ የሕይወት ቃል ሊሆን ይገባዋል ። ራሳቸውንም እየገዙ በመጠን እየኖሩ አምላካቸውን በማክበር ኅብረተሰቡን ያገለግሉ ዘንድ ይጠበቅባቸዋል ።

የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ይላል

"ዋይታ ለማን ነው ? ኀዘን ለማን ነው ?

ጠብ ለማን ነው ? ጩኸት ለማን ነው ?

ያለምክንያት መቁሰል ለማን ነው ? የዓይን ቅላት ለማን ነው ?የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን ?" ምሳ. 23 ፣ 29 -30

"ዓይኖችህ ጋለሞታዎችን ያያሉ ልብህም ጠማማ ነገርን ይናገራል." ቁ33

"መንፈስ ይሙላባችሁ እንጅ በወ

ተከታዩ ወደ ገፅ ፲፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ሥርዓተ ጸሎት

በዓለም ውስጥ ለሚከናወን ለእያንዳንዱ ድርጊት የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው ያለ ሥርዓት የሚካሄድ ተግባር ሊኖር አይችልም ከአለም ውጤቱ ሊያምርና የታሰበውን ግብ ሊያስገኝ አይችልም ዓለም ራሱ በተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት ስለሚንቀሳቀስ በእርሱ ላይ የሚከናወነው ሥጋዊና መንፈሳዊ ተግባር ሁሉ በሥነ ሥርዓት ይካሄዳል ።

በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የተፈለገው በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለሚካሄደው የጸሎት ሥነ ሥርዓት ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊትና ሐዋርያዊት እንደ መሆንዋ ፣ ሥርዓትዋም ጥንታዊና ሐዋርያዊ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትመራበት ሥርዓተ ጸሎት ክርስቶስ ለሐዋርያት ያስተማረውና ከሐዋርያት ለ318 ሊቃውንት የተላለፈው ነው ። ጸሎት መቼ በየት? እንዴት? ለማንና ለምን? እንደሚጸለይ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮአል፣ማቴ ፣15 ፣26 ፣ 40 ሉቃ 18 ፡ 9 -14

ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሱ ሊቃውንት የጸሎትን አፈጻጸም በጻፉበት ክፍ የጸሎት ጊዜያት ሰባት እንዲሆኑ ሥርዓት ሠርተዋል ። እነርሱም ሀ- ነግህ ከጥዋቱ አሥራ ሁለት እስከ አንድ ሰዓት

ለ ሠለስት ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት

ሐ ቀትር ከቀኑ ስድስት ሰዓት

መ በሰዓት ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት

ሠ ሠርክ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት

ረ ጊዜ ንዋም ሲተኙ ከምሽቱ 2-3 ሰዓት

ሰ መንፈቀ ሊሊት ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት በነዚህ ጊዜያት መድኅን ክርስቶስ ለሰዎች ድኅንነት ሲል የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራ እያስታወሱ መጸለይ እንደሚገባ ጽፈዋል አስተምረዋል በተለይ የነግህና የሠርክ ጸሎት በቤተ ክርስቲያን መፈጸም እንደሚገባቸው የታዘዘ ሲሆን የቀሩት ግን በማንኛውም ቦታ በቤትም ሆነ በመንገድ ሊፈጸም እንደሚቻል ሥርዓት ተሠርቷል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሥርዓት በመመራት በነግህ ለኪዳን ፣ በሰዓት ለቁርባን ፣ በሠርክ ለጸሎት በርዋ ክፍት ነው ። በቀሩት ጊዜያት የሚጸለየውን ጸሎት ግን ምእመናን ሁሉ እንደ እየችሎታቸው በያሉበት ቦታ እንዲጸልዩ ታዝዞአል።

በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛዎቹ በአሥራ አንድ ሰዓት የጸሎት ፕሮግራም አላቸው ። ካህናቱ ለጸሎት ይገኛሉ ለጸሎት ከሚመጡ ምእመናን ጋር ጸሎት ያደርሳሉ ። በጸሎቱም መጨረሻ የወንጌል ትምህርት ይሰጣሉ ። ይህ አይነቱ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ክርስቶስ ያስተማረውና ሐዋርያት የተቀበሉት ስለሆነ ሐዋርያዊ ሥርዓት ነው ። በነግህና በሠርክ በቤተ ክርስቲያን በማኅበር እየተሰበሰቡ መጸለይና ትምህርት ወንጌልን መስማት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ቀዋሚ ሥርዓት ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን በያለበት ቦታ እንደ ጊዜውና እንደቦታው አመችነት የክርስቶስን ሕማሙንና ሞቱን ፣ ትንሣኤውንና ዕርገቱን በአጠቃላይ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ከሞት ወደ ሕይወት ከኀሣር ወደ ክብር ለመመለስ የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ እያሰቡ መጸለይ እንደሚገባ በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጽ 14 ተብራርቶ ተወስኖአል ።

የማኅበር ጸሎት በሚጸለይበት ጊዜና ቦታ የግል ጸሎት መያዝ ከጸሎት ሥነ ሥርዓት ውጭ ስለሆነ ክልክል ነው ለምሳሌ በቅዳሴሰዓት የቅዳሴውን ጸሎት መከታተልና ተሰጥዎ መቀበል ሲገባ የግል ጸሎት ለመያዝ መጽሐፍ ዘርግቶ በማነብነብ ሌሎቹን ምእመናን የሚያስቸግሩ ጥቂቶች አይደሉም ። ቅዳሴው ቅሉ ለወንድና ለሴት ለሽማግሎችና ለሕፃናት የሚጸለይ የማኅበር ጸሎት ስለሆነ ሁሉም በንቂሐ ሕሊና በሰቂለ ልቡና ሁና ተሰጥዎውን መቀበል እንጂ ሌላ ሥጋዊ ተግባር ማሰብ ወይም የግል ጸሎት መያዝ ክልክል ነው ። ከግል ጸሎት ይልቅ የማኅበር ጸሎት ይጠቅማል ከማኅበር ጸሎት የግል ጸሎት የበለጠ እንደሚጠቅም የሚያምኑ ሰዎች ቢኖሩ ትዕቢተኞች ናቸው ። ትዕቢትም ዐቢይ በደል ስለሆነ ያስቀጣል ።

በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሚታይ ሌላም የተዘበራረቀ የጸሎት አፈጻጸም አለ፤ይኸውም በቅዳሴው መጨረሻ ላይ በአንድ በኩል " አቤቱ ሕዝብን አንድ ርስትህንም ባርክ '' በማለት ቄሱ በሚጸልይበትና ሕዝቡን በሚባርክበት ጊዜ በቅኔ ማኅሌት በኩል ዕጣን ሞገድን ለመጸንጸል የሚደናገረው የከበሮ ድምፅና የወጣቶች መዝሙር ነው ።

ከዚህ ላይ ዕጣን ሞገድ አይጸንጸል ፣ ወጣቶችም አይዘምሩ ለማለት አይደለም ። ሁሉም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በሥነ ሥርዓት ይፈጸም ለማለት ነው ። ቄሱ የሠርሆተ ሕዝቡን ጸሎት ለማድረስና ለማሰናበት ከመውጣቱ በፊት ዕጣን ሞገዱ መፈጸም ይኖርበታል ወይም ዕጣን ሞገዱ እስኪፈጸም ድረስ ቄሱ የሠርሆተ ሕዝቡን ጸሎት ከመጀመር መታገስ ያስፈልግ ይሆናል ። በማኅሌት በኩል ያለው የከበሮና የጸናጽል ድምፅ ሥራውን ሳይፈጽም በወጣቶች በኩል ሌላ መዝሙር ከተጀመረና በየስፍራው ጩኸት ከበዛ ግን የመዝሙሩ ፍሬ ሐሳብ ወይም ትምህርት ለአድማጮች ግልጥ ሆኖ ሊሰማ ካለመቻሉም በላይ ዕውቅ የሆነ ሐዋርያዊ ሥነ ሥርዓት ያላትን ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እንደሌላትና በሥነ ሥርዓት እንደማትማራ ሊያስገምት ይችላል ።

በሌላው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አንዱ ክፍል በምዕራብ በኩል ትምህርት እየሰማና መዝሙር እየዘመረ ሳለ ሌላው ክፍል በምሥራቅ በኩል ምህላ ያደርሳል ትምህርቱ ፣ መዝሙሩና ምህላው ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በንጹሕ ልቡና በትሑት ሰብእና ሁኖ በማኅበር ቢጸለይ አገርን ከጥፋት ሰውን ከሞት ይታደጋል። ግን ጻድቅ ወይም ጸሎተኛ ለመምሰል በቡድን በቡድን እየተከፋፈሉ አንዱ በምሥራቅ ሌላው በደቡብ እየሆኑ መጮኽ ግን ግብዝነት ነው በግብዝነት የሚፈጸም ጸሎትም ዋጋ ቢስ እንደሆነ በወንጌል ተነግሮአል ማቴ 6 ፣ 5 - 14።

ስለዚህ አንደኛ በቅዳሴ ሰዓት የግል ጸሎት መያዝ ተገቢ አለመሆኑን ማስረዳት ፣ ሁለተኛ በጥዋትና በማታ በቤተ ክርስቲያን የሚደረገው ጸሎተ ማኅበርና ትምህርተ ወንጌል ከአለ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ምእመናን ሁሉ የጸሎቱና የትምህርቱ ተካፋዮች እንዲሆኑ ማድረግ ፣ ሦስተኛ በእሁድና በሌሎችም የበዓላት ቀን በየቤተ ክርስቲያኑ በምህላና በትምህርት እያሳበቡ በአራቱ መዓዝነ ቤተ ክርስቲያን በመጮህ የሚያስቸግሩትን መስል ሰባክያን ሥርዓት ማስያዝና ለምእመናን ጠቃሚ ትምህርተ ወንጌል መስጠትና የቅዳሴን ፣ የመዝሙርንና የጸሎትን ሥነ ሥርዓት ማስተካከል የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ነው ። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና ካህናት በጥብቅ ሊያስቡበት ይገባል ።

ራደ አስረስ

## ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፲ የዞረ

ሙያቸው በላይ የእግዚአብሔርን ሕግና የትሩፋት ሥራን የሚያከብሩ ጻድቅ ሰው ስለነበሩ ቀደም ብለን እንደተናገር ነው በሕጋዊ ጋብቻ 6 ወንድ 3 ሴት ልጆች ያፈሩ ሲሆኑ የትሩፋት ሕ'፣ የሆነውን ሥርዓተ ምንኩስና በ1957 ዓ.ም. በደብረ ሊባኖስ ገዳም በመቀበል ቅስና ከምንኩስና አስተባብረው ይዘው ቤተ ክርስቲያንን ፍጹም በሆነ የአበው ሥርዓት አገልግለዋል ።

እኒህ ዝነኛ መምህር በልጅነታቸው ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት አደጋ ደርሶባቸው ሁለት ዓይናቸው የታወረ ቢሆንም አዕይንተ አእምሮ የተሰጣቸው ብሩህ ልቡና የነበራቸው ሰው ነበሩ ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እኔ ሩጫዬን ጨረስሁ ሃይማኖቴን ጠበቅሁ እንግዲህስ ወዲህ የእውነት ፈራጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያች ዕለት የሚሰጠኝ የእውነት አክሊል ይቆየኛል 2 ጢሞ 4 ፣ 7 እንዳለው አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ ከሀገር አገር ተዘዋውረው በአገኙት የትምህርት ፋና እያበሩ ለ70 ዓመት ያህል ከኖሩ በኋላ በተወለዱ በ98 ዓመት ዕድሜያቸው መጋቢት 22 ቀን 1973 ዓ.ም. ከቀኑ በ8 ሰዓት ከዚህ ዓለም ሃሳብና ድካም ወደ ዘለዓለም ዕረፍት አልፈዋል ።

አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ በሥጋም በትምህርትም የወለዱአቸው ብዙ ልጆች ስለአሉዋቸው ስማቸው ሕያው ነው ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

## የአልኮል መጠጥ......

ከገፅ ፲፫ የዞረ

ይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፡''
ኤፌ..5 ፡ 18

አዎ የእግዚአብሔር ቃል እስካሁን ያየናቸውን ነጥቦች ሁሉ በእነዚህ አጫጭር ጥቅሶች በማጠቃለል ያስተምረናል ። ታድያ ይህን ቃል የሚቀበሉና የሚከተሉ ሁሉ በሕይወታቸው ሊተረጉሙት የሚገባ ሆኖ እናገኘዋለን ። ለምን ቢባል በተለይ ክርስቲያኖች በተሳሳተ ጐዳና ቢሄዱ ስህተታቸው በሰው ዘንድ ጐልቶ ስለሚታይ እርእየበመሆን ፋንታ መሰናክል ስለሚሆኑ እምነትንም ያስነቅፋሉና ነው ።

በአጠቃላይ ኑሮን በእግዚአብሔር ቃል መምራት ሰላምና ደስታ እንዲሁም የአእምሮ ርካታ ሊሰጥ መቻሉ አያጠያይቅም ። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ለአልኮሆል ሱስ ተገዥ ከመሆን ራሱን ለእግዚአብሔር በማስገዛት ቢኖር ሕይወቱን ትርጉም አልባ ከሚያደርገው ጉዳት ተጠብቆ ጥሩ አኗኗር እንደሚኖር ግልጽ ነው ።

ተማሪ ነርስ የሻረግ ሥርጋዌ





www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ነፍሰ ጡሮችን በዐይናችሁ አይታችሁ ወንድ ወይም ሴት እንደሚወልዱ ለይታችሁ መናገር ትችላላችሁ?



ሴት እንደሚወልዱ ተነግሮአቸው ሴት የወለዱት ወ ሮ

እርግጥ ሐኪሞች በምርመራ እንደሚቻል ይናገራሉ እንጂ በዓይን አይቶ እንደሚ ታወቅ አይናገሩም ።

ጥበቡ መንግሥቱ ግን ከብዙ ጊዜ ልምምድና አቀማመጡንም በማጥናትና በማየት ብቻ ያረገዙ ሴቶች ወንድ ይሁን ሴት የትኛውን ፆታ እንደሚወልዱ ለይቶ አውቃለሁ ይላል ። ይህም ከዚህ ቀደም በሬድዮና በቴሌቪዥን ቀርቦ እንደነበር የሚታወስ ነው ።

ነገር ግን ጥበቡ መንግሥቱ የሚለው ነገር በቤተ ክርስቲያን አነጋገር መንፈሳዊ ስጦታ ይሆን ? ወይንስ ጥንቆላ ? የትኛው ብለን እኛም ሆን ሌሎች ስለ ተጠራጠርንና ጠይቀንም መረዳት ስለ ፈለግን ጥበቡን በሰፊው አነጋገረን የሰጠን መልስ ለአንባብያን አቅርበናል

ጥበቡ የ29 ዓመት ወጣት ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በ1970 ዓ.ም እንደ አጠናቀቀ ይናገራል ።

ትንሣኤ፡- አቶ ጥበቡ ያረገዙ ሴቶች ወንድ ይሁን ሴት ያረገዙትን የማወቅ ችሎታ አለኝ ብለሃል እንዴት ነው የምታውቀው ?

ጥበቡ ፤ - ይህንን የማውቀው ሰዎቹን (እርጉዞችን ) እመለከትና የጽንሱን የአቀማመጥ ሁኔታ በመመልከት ነው ላውቅ የምችለው ።

ትንሣኤ ፡- አቶ ጥበቡ ለመሆኑ ይህንን ጥበብ እንዴት ልታገኘው እንደቻልክ ብትገልጽልን ?

ጥበቡ ፡- አዎ ይህንን ማወቅ የቻልኩት ከብዙ ጊዜ ልምምድ በኋላ ነው ልምምዱን ማካሄድ ከጀመርኩ ወደ አራት ዓመት ያክል ሆኖኛል ። የማውቀውም ፅንሱ በማኅፀን ውስጥ ሳለ የአቀማመጡን ሁኔታ በውጭ በመመልከት ሲሆን ፤ የአቀማመጡን ሁኔታ ስመለከት ለዓራት ዓመታት ያህል ይህንን ልምምድ አካሂጀለሁና ወንድ ሲሆን እንዴት እንደሚቀመጥ ሴት ስትሆንም እንዴት እንደምትቀመጥ ለይቼ አውቄአለሁ በዚህ አኳኋን ነው ላውቅ የቻልኩት ።

ትንሣኤ ፡- ለምሳሌ ነፍሰ ጡር ሴቶች በእርግዝና ወራት የተነሱትንም ፎቶግራፍ በማየት እንደዚህ እንደምታውቅ ተናግረሃል ይህንንስ እንዴት ልታውቅ ቻልህ ?

ጥበቡ ፡- ይህም ቢሆን ያው ሰዎቹን በማየት የአቀማመጡን ሁኔታ ስመለከት ወንድ ወይንም ሴት መሆኑን እንደአረጋገጥኩ ይኸኛውም አሠራር በፎቶግራፍም ቢሆን ምንም ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል ተገነዘብኩና በፎቶ ግራፎች ይህን ግምት መግለጽ እንደምችል ተረዳሁ ።

ትንሣኤ ፡- ይህን ጥናት እንድታጠና ያነሣሣህ ምክንያት ምንድን ነው ?

ጥበቡ ፡- እስካሁን ድረስ የሌለ ለየት ያለ ስለሆነ ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትን ከማንጸባረቅ ይልቅ አዳዲስ ነገሮችን ማወቁ ጥሩ መስሎ ስለታየኝ ነው ። ለወደፊቱም እንደዚህ ለየት ያለ ነገር ለማጥናት ዓላማ አለኝ ። አሁንም እንኳ ቢሆን የተለያዩ ጥናቶችን አካሂጃለሁ ካሉትም ጥናቶች አንዱ ይህ እንደሆነና ይህም እንኳ ቢሆን ከመጨረሻው ውጤት ደርሻለሁ ብዬ አልናገርም ገና ብዙ ይቀረኛል ።


ትንሣኤ ፡- ለመሆኑ እስካሁን ድረስ ከተናገርካቸው የአስተሳሰብ ሁኔታ የተሳሳተ ነገር ገጥሞህ ያውቃል ?

ጥበቡ ፡-በእርግጥ እስካሁን ድረስ ሰማንያ በመቶ ያህል እውነተኛ ሁኗል ነገር ግን ከጥናቱ ፍጹም አለመሆን የተነሣ አንዳንድ ስህተቶችን አይቻለሁ ከተናገርሁት ውስጥ ከመቶ ሃያው አልሆነም እነርሱንም ለማረም ጥናት እያደረግሁ ነኝ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ከአመለካከቴ ሁኔታ ስህተት ቢፈጠርም ቅሉ አዲስ ነገር ሲሆን የሚችል አይመስለኝም ።

ትንሣኤ ፡- ለመሆኑ በፎቶግራፍም ሆነ ያለ ፎቶግራፍ በማየት ስንት ወር የሆናቸውን ፣ ነፍሰ ጡሮች ነው ወንድ ይሁን ሴት እንዳረገዙ መለየት የምትችለው?



ጥበቡ፡-አዎ ካረገዘች አራት ወር የሆናትን በማየት ወንድ ወይም ሴት እንዳረገዘች



ነፍሰጡሮችን ተመልክቶ ሴት ወይም ወንድ እንደሚወልዱ የሚናገረው ጥበቡ መንግሥቱ

ማወቅ እችላለሁ ። በፎቶግራቸው ግን ከአምስት ወር በኋላ መለየት እችላለሁ።

ትንሣኤ ፡- የነፍሰጡሮችን ፎቶግራፍ በምን ምክንያት ለመመርመር ጀመርክ?

ጥበቡ ፡- እንደዚህ በፊት ለፊት እያየሁ የምነግራቸው ሰዎች ቁጥራቸው እየበዛ ሲሄድና የኔም ንግግር እውነት እየሆነ ሲመጣ ጥናቴ መልካም ውጤት ሳያገኝ አይቀርም በማለትና ጥናቴ አንድ ቀን ድንገት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ቢደርስ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ሴቶችም ሆኑ በየክፍለ ሃገሩ የሚኖሩ ሴቶች ምን ዓይነት ፆታ እንደሚወልዱ ማወቅ ፈልገው ፎቶግራፋቸውን ቢልኩ እኔ የዚህ ሁኔታ ጠለቅ ያለ እውቀት ካለኝ በሚልኩት ፎቶግራፍ ላይ (በስተጀርባው )ወንድ (ሴት ) ብዬ ብልክላቸው ከመውለዳቸው በፊት ለሚያደርጉት የልጅ ስም ሆነ ሌላ ዝግጅት ይረዳቸዋል ብዬ ተስፋ በማድረግ ነው የጀመርኩት ። ይሁን እንጂ ብዙና ጠለቅ ያለ ጥናት ስለሚያስፈልገው አሁንም ጥናቱን በማካሄድ ላይ ነኝ ይህም ከሥራዬ ጋር የተያያዘ ስለሆነ በበለጠ ማጥናት እችላለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ትንሣኤ ፡- ራሳቸውን አይተህ ከነገርሃቸውና ፎቶግራፋቸውን አይተህ ከነገርሃቸው የማንኞቹ ውጤት ይበልጣል?

ጥበቡ ፡- ለጊዜው ከፎቶግራፋቸው ይልቅ ነፍሰጡሮቹን አይቼ የምነግራቸው የበለጠ ውጤት እያሳየ ነው ስለዚህም ነው በፎቶ ግራፋቸው ላይ በይበልጥ ጥናት ያስፈልገኛል ያልኩት ።

ትንሣኤ ፡- ባለፈው ጊዜ በሬድዮና በቴሌቭዥን ቀርበህ በነበርክበት ጊዜ የፕሮግራሙ አዘጋጆች ዶክተር ነቢያትን አነጋግረው ነበር እርሳቸውም በእስታስቲክ እንዲጠና እናደርጋለን ያሉ ይመስለኛል ስለዚህ ጉዳዩ እንዴት ነው?

ጥበቡ ፡- ህዝቡ የሬድዮኑና የቴሌቭዥኑን ሰምቶ ዶክተር ነብያት በሰጡት አስተያየት መሠረት በእስታስቲክስ እንዲጠና ስለተባለ ከዚያ ወዲህ በግል እየመጡ ያነጋገሩኝ ነፍሰጡሮች አሉ እነርሱም ሲወልዱ ያኔ የሚገኘውን ውጤት እንመለከታለን ።


ትንሣኤ ፡- ነፍሰጡር ሴቶች ወንድ ሴት እንደሚወልዱ ነግረኻቸው ልክ ሆኖ ሲያገኙት ምን ዓይነት አስተያየት ይሰጡሃል ?

ጥበቡ፡- ብዙ ዓይነት አስተያየት የሰጡኝ አሉ ይኸውም አንዳንዶቹ ካለማወቅ የተነሳ ይህ ጠንቋይ ይሆናል እንጂ እንዴት ሊያውቅ ይችላል ሲሉ ገሚሱ ደግሞ ይህ መቸም መንፈሳዊ ስጦታ መሆን አለበት ይላሉ ። ግን ይህ አስተያየት ልክ አይደለም ጥንቆላም አይደለም መንፈሳዊ ስጦታም አይደለም ነገር ግን ይህ ከላይ እንደገለጽኩት በራሴ ጥረት በጥናት ያገኘሁት እንጂ ሌላ ምንም ነገር እንዳልሆነ ይህንን መጽሔት ያነበበም ሆነ ስለኔ በሬድዮንና በቴሌቪዥን የሰማ ሁሉ እንዲያውቅ እፈልጋለሁ ።

ትንሣኤ ፡- ይህ ነገር በጥናት ያገኘኸው ከሆነ ሌላውን ልታስጠና ፈቃደኛ ነህ?

ጥበቡ ፡ - አሁን ለጊዜው ለማስተማር አይቻልም ምክንያቱም በሬድዮ እንደ ተነገረው ይህ ምርምር በእስታስቲክስ ተይዞ አንድ ዓይነት ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ ምርምሩ በዚሁ አይነት ይቀጥላል ።

ውጤቱ በአጥጋቢ ሁኔታ ከታየ በኋላ ግን ማንም ሰው ሊማረውና ሊያውቀው እንዲችል በትምህርት እንደሚሰጥ ተስፋ አደርጋለሁ ።



በእናቱ ማህፀን ሳለ ወንድ ሆኖ እንደሚወለድ የተነገረለት ሕፃን ይነበብ አድማሱ



www.ethiopianorthodox.org

# የነፃ ትምህርት ቤት ክርስቲያን

አንደኛዋ ቤተ ክርስቲያን ለሌላዋ ቤተ ክርስቲያን የነፃ ትምህርት የምትሰጥበት ዋናው ዓላማ የራሱዋን ባህልና ሥነ ሥርዓት ዶግማ ፡ በጠቅላላው ያላትን መንፈሳዊ አሰራር ለማስተዋወቅና ወዳጅነትንና ግንኙነትንም ለመፍጠር ነው ። የነፃ ትምህርት ዕድል ያገኘችው ቤተ ክርስቲያን ልትወጣው በማትችለው ችግር በኩል ሊቃውንትዋ ሄደው እንዲሰለጥኑና ከዚያም በትምህርት በሚቆዩበት ጊዜ ባህሉዋንና ሥነ ሥርዓቱዋን እንዲያስተዋውቁላት ፣ የተገኘውም ወዳጅነትና ግንኙነት በበለጠ እንዲጠናከር እንዲያደርጉላት ነው ።

በዚህ መንገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በእምነትና በሥነ ሥርዓት ከሚመሳሰሉዋት አብያተ ክርስቲያናት ይልቅ ፣ በአንዳንድ ጥቃቅን ነገር ከማይመሳሰሉዋት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በርከት ያለ የነፃ ትምህርት ስታገኝ ቆይታለች አሁንም በማግኘት ላይ ነች የነፃ ትምህርት ዕድል መገኘቱ አስደሳች ሆኖ ሳለ አንዳንድ ጊዜ በአመራረጡ በኩል ብርቱ ጥንቃቄ ባለመደረጉና ለከፍተኛ ትምህርት ለሚላኩ ምሁራን አንድ ዓይነት ግዴታ ባለመሰጠቱ የሚገኘው ውጤት አጥጋቢ መስሎ አይታይም ።

ይህ ሊሆን የቻለው የነፃ ትምህርት ለቤተ ክርስቲያናችን ሲሰጥ ላኩኝ እያለ ማመልከቻ የሚያቀርበውን ሳይሆን መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያኑዋ ችግሩዋ በየት በኩል እንደሆነ ማጥናት ሲገባት ማመልከቻ ያቀረበውን ሁሉ ለመላክ በማቀዱዋ እንደሆነ ይገመታል ። ይኸውም የብሉይና የሐዲስ ሊቃውንት ቢኖሩዋትም ፣ በዩኒቨርስቲ ደረጃ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ በስብከት ዘዴ በጠቅላላው በነገረ መለኮት የሰለጠኑ ሊቃውንት ስለሌሉዋት ፣ እነዚህን አጥንታ ብትልክና የነፃ ትምህርት ከመገኘቱ በፊት አዘጋጅታ ብታስቀምጣቸው ለችግሩዋ መፍትሄ እንደሚገኝና የተገኘውም የነፃ ትምህርት ግቡን እንደሚመታ አይጠረጠርም ።

የነፃ ትምህርት እንደተገኘ የሚገልጥ ማስታወቂያ ቤተ ክርስቲያኑዋ ስታወጣ የሚያውቁዋትም የማያውቁዋትም ሁሉ የነፃ ትምህርት ዕድል ለማግኘት የፈተናውም ተሳታፊ ለመሆን ይሯሯጣሉ ብቁ ሆኖ ለመገኘትም የቅኔ ፣ የመጻህፍት ትርጓሜ የድጓ የዝማሬ መዋሥዕት ፣ የአቋቋምና የቅዳሴ ወዘተ መምህር ነኝ የሚል መረጃ ያቀርባሉ መረጃው ያላስደሰታቸው ከአጣሪ ኮሚቴዎች አንዳንዶቹ ልሂድ ያለው ሁሉ እንዲሄድ ካልተፈለገ ፣ የቤተ ክርስቲያን ችግር ያቃልላሉ ተብለው እምነት የተጣለባቸው በጠባዩም በትምህርትም የተስተካከሉትን ምሁራንን ለመምረጥ ከታሰበ የቀረበው መረጃ ልክ አይደለም ። እውነተኛ መረጃ ማለት በየትምርት ቤቱ በሚማሩበት ጊዜ ከነማን ጋር እንደተማሩ ፣ የደብሩ ካህናትና ምዕመናን የሚያውቁዋቸው መሆኑን መምህሩ ከሰጣቸው ወረቀት ላይ የደብሩም ማህተም አብሮ ሲቀርብ ነው የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ በዚህ አስተሳሰብ መፈጸሙ ይቅርና ሁኔታው በድምጽ ብልጫ ስለማያልፍ እንደታሰበው ሳይሆን ይቀራል ።

እንከን ባልተቀላቀለበት አሠራር ይፈጸም ቢባል እውነተኛ ምሁራንን ለማግኘት በየሙያቸው በየቤተ ክርስቲያኑ ሲያገለግሉ ሲቀድሱ ፣ ሲሰብኩና ሲዘምሩ ምእመናን ስለሚያውቁዋቸው ይህ እራሱ በቂ መረጃ ሊሆን ይችላል የሚላኩ በንጽህና ቸው በወንጌላዊነታቸው፣ በጠባያቸው ፣ በሕዝብ መካከል የተናገሩትን በተግባር የሚገልጹ ለምሳሌ አትስከሩ ብለው ራሳቸው የማይሰክሩ ፣ አትስስኑ ብለው እራሳቸው በዚህ ወራዳ ተግባር የማይጠረጠሩ ፣ ለራሳቸው ሊያደርጉላቸው የሚወዱትን ለሌላው ማድረግ የሚወዱ ካህናት ይህ አሠራር ከሞያቸው ጋር ሊመዘን ይገባዋል ።

ምንጊዜም ቢሆን ለቤተ ክርስቲያንዋ የሚጠቅም ካህን እንላክ ከተባለ እስከ አሁን በተጠቀመው/መመዘኛ ብቻ ተወስኖ ሳይቀር የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ሕግና ሥርዓት የአባቶችን መንፈሳዊ ባህልና ልማድ አጠናቆ ያወቀ ሆኖ በዚህ ረገድ ተጠይቆ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚችል መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ለመላክ ከውድድር ውስጥ ከማስገባቱዋ አስቀድማ ልትረዳ ያስፈልጋታል ።

አንድ ሰው በቁመናው ፣ በውበቱ፣ በአለባበሱ በወገንና በአካባቢው ብሎም ለግላዊ እድሉ የሚያበቁ መለኪያዎችን ማሟላትና በቀረበለት መመዘኛዎች ሁለትሦስቱን ያህል ጥያቄዎች በመመለስ ብቻ ለዚህ እድል በመብቃቱ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅማትን ካህን ላከች ለማለት አያስደፍርም።ምክንያቱም በመልካም ጠባይ ሳይሆን በልዩ ልዩ አመራረጥና ፈተናውን በመሸምደድ በማለፉ ነው ።

እዚህ ላይ አንድ የግብረ ገብ አስተማሪ ለተማሪዎቹ የተናገረውን መመልከት ይጠቅማል አስተማሪው ለተማሪዎቹ ፈተናሰጥቶ ጥሩጠባይ የሌላቸውናበክፍልውስጥየሚበጠብጡተማሪዎችበፈተናው 99 %ሲያገኙበጥሩጠባይናበትህትና የታወቁት ተማሮች ግን 60% አገኙ ከዚህ በኋላ አስተማሪው ተማሪዎቹን ሰብስቦ የግብረ ገብ ትምህርት ውጤት በመልካም ጠባይ የሚሰጥ እንጂ በሽምደዳ የማይሰጥ ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲህ በጠባይ እንጂ በፈተና አልሰጥም አለ ይባላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ወደ ውጭ የምትልካቸው መምህራን ከላይ እንዳስረዳነው ፈተናውን በልዩ ልዩ ምክንያት አለፉ በማለት ብቻ ሳይሆን በጠባያቸው በቀና አገልግሎታቸው እውቀታቸውና ተምረው ሲመለሱ የበሉበትን ወጭት ሰባሪዎች ሳይሆኑ ለቤተ ክርስቲያን ብለው የሚያስቡ ናቸው ብላ የምታምንባቸው ሊሆኑ ይገባል ።

ተከታዩን በገጽ ፳፭ ይመልከቱ



# የአባለዘር በሽታ በሰውነት ላይ የሚያስከትለው ችግር



ተማሪ ነርስ ልዕልት ረታ

የአባለዘር በሽታ ዝሙት ከሚያስከትላቸው ጠንቆች አንዱና በጣም ከባድ የሆነው ነው ። በልማድ አንዳንድ ሰዎች ይህ በሽታ ሊይዝ የሚችለው ወደ ፀሐይ ወይም ወደ ጨረቃ ዞሮ በመሽናት ነው በማለት ይናገራሉ ይሁን እንጂ ይህ ትክክለኛ ያልሆነ አባባል ነው ። በሽታው በሰዎች ዘንድ ሊዘምት የሚችለው በግብረ ሥጋ ግንኙነት መሆኑ ተረጋግጧል ይህ በሽታ በማንኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎችን ይይዛል በጣም የሚበዛው ግን በወጣቶች አካባቢ እንደሆነ ይነገራል ። በዓለም ላይ ያሉ የአባለዘር በሽታ ዓይነቶች ብዙ ናቸው ። በሀገራችን የተለመዱት ና ጐልተው የሚታዩት ግን ቂጥኝና ጨብጥ በመባል የሚታወቁት ናቸው ። ከዚህ ቀጥሎ እነዚህ በሽታዎች በሰውነት ላይ የሚያስከትሏቸውን ልዩ ልዩ ጉዳቶች እናያለን ።

በመጀመሪያ ቂጥኝን ብንመለከት ምንም እንኳ በበሽታው ከተበከሉ ነገሮች ጋር በመነካካት አንዳንዴ ሊይዝ ቢችልም አብዛኛውን ጊዜ ሰዎችን የሚበክለው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ነው ። በሽታው በጣም አደገኛ በመሆኑ በዋና ዋና የሰውነት ክፍሎች እንዲሁም በደም ቧንቧዎች ላይ የማይድን ጠንቅ ጉዳትን ያስከትላል ። ይህ በሽታ ሦስት ዓይነት ደረጃዎች አሉት ። በመጀመሪያው ደረጃ በወንድም ሆነ በሴት ብልት ላይ ከባድና በቀላሉ የሚደማ ቁስል ይፈጥራል ። በዚህም ምክንያት በአካባቢ ያሉ እጢዎች ያብጣሉ ። እንዲሁም እልፎ እልፎ በከንፈርና በጣት ላይ ቀለል ያሉ ቁስሎች ይታያሉ ። በተወሰኑ ሳምንታት ውስጥ ቁስሉ ይጠፋና ሁለተኛው ደረጃ መታየት ይጀምራል ። በዚህ በሁለተኛው ደረጃ በሽታው በደም ውስጥ ይሰራጭና ባጠቃላይ በሰውነት ውስጥ በመዘዋወር የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን መበከል ይጀምራል ። በቆዳ ላይ የሚያሳክክ የሰውነት መንደብደብ ይታያል ። በሰውነት ውስጥ ያሉ እጢዎች ባጠቃላይ ያብጣሉ የአፍና የምላስ መቁሰል እንዲሁም የጸጉር መርገፍ የመሳሰሉት ነገሮች ይታያሉ ። ሌላም ደግሞ የደም ማነስና በአንጐል አካባቢ በሚገኙ የደም ቧንቧዎች ውስጥ ጠባሳ በመፍጠር ደም በሚገባ እንዳይዘዋወርና የአንጐል ሴሎች በቂ የሆነ የደም መጠንብ እንዳይደርሳቸው ያደርጋል ። በዚህ ሁኔታ ህመሙ ከሁለተኛው ደረጃ ወደ ሦስተኛ ደረጃ ይተላለፋል ። በዚህ ደረጃ በሽታው በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ ዋና ዋና የአካል ክፍሎች ላይ ከባድ ጉዳትን ያስከትላል ። በእግር ቆዳ ላይ በጣም ጥልቅ የሆነ ቁስል ይፈጥራል በአጥንት ላይም ከባድ ህመም ያመጣል ። እንደዚሁም በልብ አካባቢ የሚገኙትን ደምን ከልብ ወደ ውጭ ለማስወጣትም ሆነ ወደ ልብ ለማስገባት የሚቆጣጠሩትን ቫልቦች በማድከምና በማላላት ደም በሚገባ እንዳይሰራጭ ያደርጋል ። እንደዚሁም ደግሞ የስሜት ሥሮችን በመጉዳት የሰውነት መስለልወይም ሽባነትን ያስከትላል በአፍ በምላስና በጉሮሮ አካባቢ ከባድ ቁስልን ይፈጥራል ከዚያም አልፎ የአፍንጫና የፊት አጥንቶች እንዲሰበሩ ያደርጋል ።

የዚህ በሽታ ሌላው የመተላለፊያ መንገድ በበሽታው የተበከለች እናት በምታረግዝ ጊዜ በማኅጸን እንዳለ ሕፃኑን ይይዘዋል ። ይህ በእውነቱ ከእናትየዋ ይልቅ በሕፃኑ ላይ በጣም ከባድ ጉዳትን ያመጣል ። ሕፃኑ ሞቶ ሊወለድ ይችላል ዓይነ ሥውር ሆኖ ሊወለድ ይችላል ፣ ወይም ደግሞ አስተሳሰበ ጐደሎ ሊሆን ይችላል ባጭሩ እንግዲህ በሽታው ቶሎ ካልታከመ እነዚህንና ሌሎችንም ዓይነቶች ችግሮች ሊያስከትል ይችላል ።

በሁለተኛው የምንመለከተው ደግሞ ጨብጥ በመባል የሚታወቀውን የአባለዘር በሽታ ዓይነት ነው ፤ ይህም እንደዚሁ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ይተላለፋል ። በመጀመሪያ በወንዶችም ይሁን በሴቶች ውስጣዊ የብልት ክፍል የማበጥና የማቃጠል ስሜት ይፈጥራል ከዚያም በወንዶች ላይ የሽንት መሽኛ ቧንቧዎች እንዲጠቡ በማድረግ ለመሽናት ከባድ ችግርን ያስከትላል ። በሴቶች ላይ ደግሞ በማህጸን ውስጥ ያሉትን የዘር መተላለፊያ ቧንቧዎችን በማጥበብ እንዳይወልዱ ያደርጋል ።

በሌላም በኩል በበሽታው የተበከለች እናት በምትወልድበት ጊዜ ጥንቃቄ ካልተደረገ በመነካካት የበሽታው መነሻ ምክንያት የሆነው ነገር ወደ ህፃኑ ዓይን በመግባት ከባድ ህመምን ያስከትላል ቀጥሎም በሽታው በቀላሉ ካልታከመና እየባሰ ከሄደ የህፃኑ ዓይን እውር ከመሆን ደረጃ ይደርሳል ። ብዙዎች ይህን በሽታ ለመደበቅ ይሞክራሉ ነገር ግን በሰውነት ውስጥ በቆየ ቁጥር ከባድ ጉዳትን እያስከተለ እንደሚሄድ ተመልክተናል ። በበሽታው ከተያዙ በኋላ ከመጨነቅ ወይም በሰውነት ላይ ከባድ ጉዳትን ከማስከተል ይልቅ ለዚህ ነገር ዋና ምክንያት የሆነውን ዝሙትን መዋጋት የተሻለ ነው ። ለዚህ በሽታ መከላከያው የክርስቲያኖች የአንድ ላንድ ጋብቻ መሠረት ሀሳብ እንደሆነ የህክምና ባለሙያዎች ያስተምራሉ ።

የእግዚአብሔር ቃል ዝሙትን እንዲህ በማለት ይቃወማል ለቅዱሳን እን



www.ethiopianorthodox.org

ይሚገባ ግን ዝሙት ርኩስት ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶአይሰማ ይህን እወቁ አመንዝራም ቢሆን ወይምየሚመኝእርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስትየለውም።ኤፌ፥5፥3-5 ዝሙት በሰውነት ላይ ይህን የመሰለ

ጠንቅ ከማስከተሉም ሌላ በሕብረተሰባችን ውስጥ በብዙ ቤተሰቦች ውስጥ ከባድ ብጥብጥ የሚያስነሳና እንዲሁም የቤተሰቡን የኑሮ መሠረት የሚያናጋ እንደሆነ እንመለከታለን ። ክርስቲያኖች ይህን ነገር በቀላሉ አያልፉትም ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች እንዲህ በማለት ያስተምራቸዋል ።

"በጌታ በኢየሱስ የትኛውን ትእዛዝ እንደሰጠናችሁ ታውቃላችሁና ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ከዝሙት እንድትርቁ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አህዛብ ከፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ አስቀድመን ደግሞ እንዳልናችሁና እንደ መሰከርንላችሁ ጌታ ስለዚህ ነገር ሁሉ የሚበቀል ነውና ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ። ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና" 1 ተሰ 4-2-7

ስለዚህ ሐዋርያው እንዳለው ሰውነትን በቅድስና መጠበቅ ማንኛውም ሰው በዚህ አሰቃቂ በሽታ ከመያዝ ሊከላከለው እንደሚችል አያጠራጥርም።

ተማሪ ነርስ ልዕልት ረታ

# የምድር ጨው ናችሁ

"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል ? ወደ ውጭ ተጥሎ ከመረገጥ በቀር ወደፊት ለምንም አይጠቅምም" ማቴ 5 ቁ 13

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተናገረው የጨው ጥቅም ምን ያህል ቢሆን ነው ?

ጨው ለሰውነት ከሚያስፈልጉት ጠቃሚ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው በመሆኑም የሰው ልጆች በተለያየ ጥቅም ላይ ያውሉታል ። ምግብን በማጣፈጥ ጥሩ ጣዕም እንዲኖረውና ሳይበላሽም ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ ይረዳል በቂ ውኃ ለመጠጣት ይገፋፋል ። በሰውነታችን ውስጥ በቂ ውኃ መኖሩ የሆድ ድርቀትም ሆነ ጠቅላላ የሰውነት ድርቀትና ክሳት እንዳይኖር ይከላከላል፤

ጨው ትክክለኛ የደም መጠን እንዲኖርና በሚገባ ተጣርቶ እንዲዘዋወር በማድረግ የሰውነት ሴሎች የተሟላ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ይረዳል ።

የጨው ዓይነቶች የተለያዩ በመሆናቸው ሌላም ዓይነት ጥቅም ይሰጣሉ ። ይኸውም የሰውነትን ጡንቻዎች በተለይም የልብን ጡንቻ ጠንካራ በማድረግ ልብ በትክክል እንዲመታ ያደርጋል ። ኖችም ሥራቸውን በሚገባ እንዲያከናውኑ ይረዳል ። ለአጥንትና ለጥርስ ጤንነትና ጥንካሬ ይሰጣል ይህ በይበልጥ የሚጠቅመው ጥሩ ውጤትም የሚያስገኘው ለእርጉዞችና ለሚያጠቡ ሴቶች እንዲሁም ለልጆች ነው ።

በዚህ አንፃር ክርስቲያኖች በምድር ላይ በሚኖሩበት ጊዜ የጨውን ጠባይ በመያዝ አልጫውን ዓለም ማጣፈጥ አለባቸው ። በተበላሸና ባልተስተካከለ ጐዳና የሚሄዱትንም መመለስና ከኃጢአት በሽታ እንዲጠበቁ ማድረግ ይገባቸዋል ። ይህንንም ሊያደርጉ የሚችሉት የእግዚአብሔርን ቃል በአረማመዳቸው በመስበክ ነው ። በኀዘን በችግር በፈተናና በጭንቅ የባዘነውን ግለሰብ ሕይወቱን ከመራራነት ወደጣፋጭነት መቀየር የሚገባ ነው ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች ለዓለም ከጨው የበለጠ ጥቅም ይጠበቅባቸዋል ። ሰዎች ሁሉ የሕይወት ውኃ የሆነውን ክርስቶስን እንዲጠሙ ማድረግ አለባቸው እነርሱ ጠጥተው የሚረኩበትን የሕይወት ውኃ ሌሎች እንዲጠቀሙበት ቢገፋፉ በጣም ጥሩ ውጤት ይኖረዋል ።

ይህ የሕይወት ውኃ በዕለታዊ ኑሮአችን ለሰውነታችን ውስጥ የተለያየ ተግባርን ለመፈጸም ከሚያስችለን ውኃ የተለየ ነው ።

ጌታችን ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል ፣ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ግን ለዘለዓለም አይጠማም እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል ሲል ለሳምራዊቷ ሴት ተናግሯል ። ዮሐ. 4-13-14

ተማሪ ነርስ የሻረግ ሥርጋዌ



# ድንግል ማርያም በቃና ዘገሊላ

ገሊላ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የትውልድ ሀገርዋ ነው ሀገርዋ መሆኑንም ወንጌላዊው ሉቃስ በ1ኛ ም. በ26ኛው ቁጥር ሲገልጽ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ክሊላ ከተማ ስምዋ ማርያም ወደምትባል ወደ አንዲት ድንግል ተላከ ሲል ገልጾዋል ። አንድ ጊዜ በገሊላ አውራጃ ውስጥ በተለይ ቃና ተብላ በምትታወቀው መንደር ሰርግ ተደረገ ባለ ሰርጉ ብዙ ሰዎችን ከመጥራቱም በላይ እመቤታችንንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቷቸው ነበር ወደ ሰርጉ የታደሙት ሰዎች የተዘጋጀላቸውን መብልና መጠጥ ሲጋብዙ በመካከል የወይን ጠጅ አለቀ የወይን ጠጅ በማለቁም ሰርግ ያደረገው ሰው የሚደዘውንና የሚጨብጠውን አጥቶ በከፍተኛ ሐፍረት ተሸፍኖ ሳለ እመቤታችን ድንግል ማርያም የወይኑን ማለቅና የሰውየውን ችግር በጸጋ በማወቅዋ ማንም ሳይነግራት ጠጅ እኮ አልቆ ባቸዋል ። ስትል ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነገረችው እመቤታችን ማርያም ጠጅ እኮ አልቋል ማለትዋ እንዲሁ አልነበረም በሰው ልጅ ላይ በሚደር ሰው ችግር ምን ያህል እንደምታዝንና ወሰን የሌለው ርኅራኄ እንደ ምትራራ ያስገነዝባል ።

እንዲያውም እመቤታችን ድንግል ማርያም የወይን ጠጅ ማለቁን አይታ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነግራ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ያስለወጠችውን አብነት በማድረግ ችግራችንን የምታስወግድልን አማላጃችን ናት ብለን እንመካባታለን ይሁንእንጂእመቤታችንቅድስትድንግልማርያም ወይንከአልቆአልባለችው ጊዜ ጌታችን ኢየሱስክርስቶስ የሰጣት መልስ አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ " የሚል ነበር ይህም አባባል ከአንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ ወይስ እናቴ የነገርሽኝን ላልፈጽምልሽ ሰው ሆንሁን ማለት ነው የዚህም አይነት አነጋገር እንግዳ ነገር አይደለም በሁሉም ዘንድ የተለመደ ነው ። አንድ ሰው ችግር ሲያጋጥመውና ችግሩም በዘመድ በወንድም የሚወገድና መፍትሔ ያገኛል ብሎ የሚያምነው ከሆነ ከቅርብ ዘመዱና ከሚወደው ጓደኛው ዘንድ ሂዶ የደረሰበትን ችግር ሲነግራቸው ታድያ ምን አለው ብለህ ነው ምንስ ያስቸግርሃል ምንምአይደለም እንደሚሉትና ደርሶበት የነበረውን ችግር ተባብረው እንደሚያስወግዱለት ሁሉ እመቤታችንም የወይን ጠጅ ማለቁን ስትነግረው ካንቺ ጋር ምን አለኝ ማለቱ ከዚህ የተለየ አነጋገር አይደለም ።

እመቤታችን ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከነገረችው በኋላ ሌላ አልተናገረችም አሳላፊዎቹን በሉ ያዘዛችሁን ሥሩ አለቻቸው ይኸውም ሳያጐድል ለሁሉ የሚሰጥ የተጠማውን ሁሉ የሚያረካ ፍጥረቱን ሁሉ ባለመዘንጋት የሚያስብ ከማያልቀው ገንዘቡም የሚሰጥ መሆኑን በማመን ነው ።

አገልጋዮችም እንደታዘዙ በዚያ ሥፍራ ስድስት የድንጋይ ጋኖች ስለ ነበሩ ጋኖቹን ውኃ ሞሏቸው ከሞሏቸውም በኋላ በሉ አስቀድማችሁ ለምርፋቁ አለቃ አቅምሱት አላቸውና የምርፋቁም አለቃ ያነን ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውኃ ቀምሶ እጅግ ተደነቀ ነገር ግን የምርፋቁ አለቃ የወይን ጠጁን ቀምሶ በጣዕሙና በመዓዛው ቢደነቅም ከየት እንደመጣ ማን እንደጠመቀው አያውቅም ነበር ።

ይህ በእመቤታችን አማላጅነት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም ከሃሊነት ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውንም በመቅመስ የተጠራው ሕዝብና ደቀመዛሙርቱ የክርስቶስን ክብር አይተው አደነቁ የባሕርይአምላክነቱንምአመኑ።ይህም ተአምር የመጀመሪያ ተአምር ነበር ።

ይህ ሰርግ ያደረገው ሰው ችግር ያጋጥመኛል የሚል በሐሳቡ አልነበረም የሚበቃውንም ያህል አዘጋጅቶ ነበርና ነገር ግን ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እንግዶችን መቀበል አትርሱ በዚህ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች መላእክት መሆናቸውን ሳያውቁ የመላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና ዕብ. 13 ፥ 1 - 2 ሲል እንደ ተናገረ ይህ በቃናስርግ ያደረገውም ሰው ጌታችንና እመቤታችንን ወደ ሰርጉ የጠራቸው በባህሉ መሠረት እንጂ የኀደለውን ይሞሉልኛል ጥቂቱንም ያበረክቱልኛል በሚል እምነት አልነበረም ይሁን እንጂ እመቤታችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ባይጠራቸው ኑሮ ይህን ታላቅ ተአምራት ለማየት ባልበቃም ነበር ።

ዛሬም ክርስቶስን በእምነት የሚጋብዙ ሁሉ ክርስቶስ ወደ እነርሱ ለመምጣት ፈቃደኛ ነው "እነሆ እኔ ከደጅ ቆሜ በር አንኳኳለሁ የሚከፍትልኝ ቢኖር ወደርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ ይላልና ።"

ከንጉሬ ርግብ ማርቆስ

## የነፃ ትምህርት...

ከገዕ ንድ የዞረ

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሲደረግ እንደቆየው የመውጫው በር አንድ ሆኖ ሳለ ሁሉም በየወገኑና በየቋንቋው የሚሾልክበት መስኮትና ቀዳዳ በመብዛቱ ካህኑ የሚላከው በሥልጣን ክህነቱናበቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሙያው ሳይሆን በደጅ ጥናቱ በእጅ አነሳሱ ፣ ንግግር በማሳመርና አማላጅ በማብዛቱ ነው ከተላኩም በኋላ ከጥቂቶቹ በቀር አብዛኞዎቹ ቀዳዳ እየፈለጉየትም ከመባከን በቀር ለመመለስ ፈቃደኞች አይሆኑም ይህም በመሆኑ የተገኘው የነፃ ትምህርት ለግለሰቦች እንጂ ቤተ ክርስቲኒቱን ሙሉ በሙሉ እንዳልጠቀማት በግልጽ እንረዳለን ።

ይህ እንዳይሆን ከተፈለገ በቤተ ክርስቲያኒቱና የነፃ ትምህርት አግኝተው ወደ ውጭ በሚላኩት ተማሪዎች መካከል አንድ የጠበቀ ውል ሊኖር ይገባል ለምሳሌ ትምህርቱ አምስት አመት ይ



www.ethiopianorthodox.org

ወስዳል እንበል የትምህርቱ አመት ሲያልቅ በውሉ መሰረት የተላኩት ተማሪዎች ወደ ሀገራቸው ተመልሰው የላኩቻቸውን ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ማገልገል ይኖርባቸዋል የተሰጣቸውን የትምህርት ዓመት ከጨረሱ በኋላ ሳይመለሱ ቢቀሩና የላኩቻቸውን ቤተ ክርስቲያን መረማመጃ በማድረግ አላማ ቸውን ቢለውጡ ውሉን እንዳፈረሱ ቢቀጠሩ ሥራው ያምር ነበር ቤተ ክርስቲያኒቱም ብትሆን በየጊዜው መቆጣጠር ሲገባት ለመጀመሪያ ከሰጠችው ከነፃ ትምህርት ገደብ በኋላ በዚያው ሲቀልጥ ዝም ብላ መመልከት ተማሪውን ለአገልግሎት እንዳልፈለገችው ያስቆጥራታል ይህም ውሉዋን እንዳልጠበቀች ግልጽ ሆኖ ያሳያል ።

ይህንንም የሚያጎላው በአሁኑ ጊዜ ከ45 በላይ ተማሪዎች በውጭ ሀገርይገኙሉ ጥቂቶች በሄዱበት መስመር ትምርታቸውን እያካሄዱ ሲገኙ በርከት ያሉ ደግሞ የሄዱበትን አላማ ለውጠው ለግላቸው የሚጠቀሙበትን ትምህርት ይማራሉ ግማሾቹም በዚያው ባሉበት አገር በሥራ እንደተሰማሩ ይነገራል ።

ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ከላይ እንደተነገረው ቤተ ክርስቲያኒቱ በየጊዜው ባለመቆጣጠሩ ዋና ተማሪው በመጨረሻ እንዲመጣ ጥሪ ባለመድረጉዋ ነው ። ችግሩ ይህ ብቻ አይደለም መጀመሪያም በሚላኩበት ጊዜ የነፃ ትምህርት ከተገኘ ተብሎ ማመልከቻ ያቀረበውን ሁሉ ከመላክ ይልቅ የሚፈልጉበት ሥራ መኖሩን መረዳት ፣ ተምረውም ሲመለሱ ወዲያው በሥራ እንዲመደቡ ቢደረግ ኖሮ ይህ ሁሉ ችግር ሊፈጠር ባልቻለም ነበር ።

ችግሩም የሚፈጠረው ተምረው ከተመለሱ በኋላ ስራ አጥተው ስለሚጉላሉና ችግርም ስለሚደርስባቸው አላማቸውን የሚለውጡትና በተማሩበትም አገር ሥራ ለማግኘት የሚገደዱበት በሁለቱ መካከል ያለው ውል ባለመጠበቁ ይመስላል ።

ይህ ችግር እንዳይደጋገም ቤተ ክርስቲያኒቱ ልሂድ ያለውን ከመላክ ይልቅ ችግሩዋን ያሟላሉ ብላ የምታምንባቸውን መላክና ሲመለሱም ሥራ አዘጋጅታ መቆየት ይፈለግባታል ይህን ካደረገች ሁሉም ወደ እርሱዋ ይመጣሉ ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



ወይዘሪት ዘነበች አድነውና አቶ ወ ሥላሴ ታደሰ መስከረም 10 ቀን 1974 ዓ.ም. በቅድስት በአታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕጋዊ ጋብቻቸውን በተክሊል በቅዱስ ቁርባን እንደፈጸሙ ።



ወጣቶቼ በቤተ



ክርስቲያን

በወጣትነትህ ወራት

ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድምአገኘሁ

# ወጣት መነኮሳት

ምንኩስና የምናኔ ሥርዓት ሲሆን ቆቡም የምናኔ ምልክትና የክርስቶስ አክሊለ ሦክ ምሳሌነው።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ « ዓለም በኔ ዘንድ ምውት እንደሆነች እኔም በዓለም ዘንድ ምውት ነኝ ሲል እንደጻፈውሁሉመነኮሳትም በምናኔ ከዓለማዊ ነገር የመለየታቸውና በዓለምም ዘንድ የሞቱ ለመሆናቸው ምልክት ይሆናቸው ዘንድ የመግነዝ ምሳሌ የሆነውን ቅንዓተ ዮሐንስ አድርገው ይታያሉ ይህም በዚህ ዓለም ተውጠው ልጄ ፣ ወላጄ ፣ ሀብቴ ወገኔ ፣ ዘመዴ፣ወዘተ በማለት ክርስቶስን ከመከተል ወደ ኋላ እንዳይሉ በምናኔ ሕግ ጸንተው ፈጣሪያቸውን ለማገልገል እንዲችሉ ነው ።

በመሠረቱ የምንኩስና ጀማሪዎች እንጦንስና መቃርስ መሆናቸው ቢታወቅም ምንጩ ወንጌል እንደሆነ የተረጋገጠ ነው ። ይህም በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10 ላይ ተጠቅሶ የሚገኝ ነው በወንጌል ሕግ ላይ የተመሠረተ ለመሆኑም ብዙ ማስረጃዎች እናገኛለን ።

ለምሳሌ አንድ ሀብታም ወጣት ወደ ጌታ ቀርቦ መምህር ሆይ የዘለዓለምን ሕይወት እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ ? ብሎ ቢጠይቀው ዐሥርቱ ቃላትን እንዲጠብቅ ነገረው ወጣቱም ሀብታም ይህንንማ ገና ከህፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄያለሁ ጎግሞስ የሚጎድለኝ ምንድነው? ቢለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልሶ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ መጥተህም ተከተለኝ አለው ። ጎበዙም ብዙ ንብረትና ሀብት ስለነበረው እያዘነ ሄደ ይላል ማቴ . 19፡ 16 - 22 ። ይህ ትምህርት ምናኔን የሚያመለክት በመሆኑ ብዙ ሀብት የነበረውን ያንወጣት እንዳላስደሰተው እንመለከታለን በሌላ በኩል ደግሞ « ከኔ ይልቅ እናት አባቱን የሚወድ የኔ ደቀ መዝሙር ሊባል አይገባውም » የሚለውና « በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንምተሸክሞ ይከተለኝ» በማለት ጌታችን የተናገረው ቃል ስለዚህ ስለምናኔ ሁኔታ የሚያጠናክር ተጨማሪ ትምህርት ነው ።

ሌላው ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ . 7 ፣ 1 - 2፣6 - 8 ፣ በጻፈው መልእክቱ ስለጋብቻ ሲያስረዳ ስለጻፋችሁልኝ ነገር ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው ። ነገር ግን ስለዝሙት ጠንቅ ለያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለያንዳንዲቱ ደግሞ ለራሰ ባል ይኑራት ... ዳሩ ግን ይህንን እንደፈቃድ እላለሁ እንጂ እንደትእዛዝ አይደለምሰው ሁሉእንደእኔ ሊሆን እወዳለሁና ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የፀጋ ስጦታ አለው ፣ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ እንደኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው በማለት የድንግልና ኑሮ ለመንሳዊ ሕይወት ከሁሉ የበለጠ መልካም መሆኑን ጠቁሟል ። ስለዚህ ብዙዎች አባቶች ድንግልናዊ ሕይወትን ስለሚመርጡ በምንኩስና ና በተባሕትዎ ለመኖር ወስነው ይመነኩሳሉ እስከ መጨረሻውም በዓላማቸው ጸንተው ክርስቶስንበመከተልሕይወታቸውንያሳልፋሉ ። ለዚህም በየገዳማቱ ቋርፍ ፣ ዳቢና ንፍሮ ብቻ በተወሰነ ሰዓተ እየቀመሱ በጸሎትና በልዩ ልዩ ተግባራት ተጠምደው ፈጣሪያቸውን የሚያገለግሉትና በበረሃ ወድቀው ቅጠል እየበሉ የሚጸልዩት በከተማም ቢሆን በዓለማቸው ጸንተው ወንጌልን እያስተማሩ ና ምእመናንን እያበዙ የሐዋርያትነት ተግባራቸውን ሳያቋርጡ የሚኖሩት አበው መነኮሳት ታላቅ ምሳሌዎች ናቸው ።

በአንፃሩ ደግሞ በዓላማው አምነው በት በምናኔ ለመኖር ወስነው ሳይሆን ለቀን መግፊያ ወይም ወቅታዊ በሆነ ጠባብ አስተሳሰብ ለጊዜው ብቻ በገዳማቱ ውስጥ የሚገኙት መነኮሳት የሚያገኙትን ጥቅም ለመካፈልና ወደ ከተማም ወጥተው ለመሾምና ለመሸለም፣ ከዚህምሌላሥራጠልሆነውበብሕትውናስም እያጭበረበሩ ና እያታለሉ ለመኖር አቅደው የሚመነኩሱና በምንኩስና ስም የሚነግዱ በኋላ ግን አማራጭ ዕድል



www.ethiopianorthodox.org

ሲያገኙ ቆባቸውን አውልቀው በመጣል ላይ የሚገኙ እንዳሉ በገሐድ ለማወቅ ተችሏል ።

በዚህ ረገድ አብዛኛውን ጊዜ ስሕተት የሚፈጠረው በወጣትነታቸው ከሚመነኩሱት መነኮሳት መካከል እንደሆነ ከሁኔታው ለመረዳት ከመቻሉም በላይ በተጨባጭ ሁኔታ ያየነውንና የተረዳነውን መነሻ በማድረግ መመስከር እንችላለን ። በሕፃንነት እድሜያቸው የሚመነኩሱ መነኮሳት ራሳቸውን ያልቻሉ ዓቅማቸውን መጥነው ያላወቁ በመሆናቸው በዚያውም ላይ ሥርዓተ ምንኩስንና በሚገባ ስለማ ያጠኑና በእድሜያቸው እየበሰሉና አካለ መጠን እየደረሱ ሲሄዱ ያ የወጣትነት ጠባያቸው ተለውጦ ከመናኝነት ወደ ዓለማዊነት ይመለሳሉ በመጀመሪያ ጊዜ ያገኙትን መንፈሳዊ ጸጋና ክብርም ያጣሉ በዚህም ሁኔታ ሕገ ምንኩስናን ከማስናቃቸው በላይ ራሳቸውን አዋርደው ቤተ ክርስቲያናቸውን እስከማስነቀፍ ይደርሳሉ ። በድንግልና ለመኖር ቃል ገብተው ከመነኩሱ በኋላ ዓላማቸውን ስተው የገቡትን ቃል ኪዳን በማፍረሳቸውና ከመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ውጭ በመሆናቸው ይህ ድርጊታቸው እነሱን ብቻ ሳይሆን በእጃቸው የቆረቡትንና በትምህርታቸው ያመኑትን ሁሉ ከማሳፈሩም በላይ ለብዙዎቹ ምእመናን መሰናክል እንደሚሆን የተረጋገጠ ነው ።

እርፍ ይዞ ወደኋላ መመለስና ማረስ እንደማይቻል ሁሉ ከምንኩስና በኋላም ወደ ዓለም መመለስ ከሁለት ዛፍ መውደቅ ነው ። ማንም ሰው የተፋውን መልሶ መቀጥ እንደማይቻል የታወቀ ነው ስለሆነም ምርጫ ከምንኩስና በፊት እንጂ በኋላ አይደለምና ማጥናት ፣ ማሰብና መወሰን የሚያስፈልገው በመጀመሪያ ስለሆነ ከመነኩሱ በኋላ መልሰው የሚያፈርሱና እንደገና የኃጢአት ተገዥ የሚሆኑ ሁሉ የተፉትን መልሰው የሚልሱ ናቸው ።

ስለዚህ ዋናው መንስኤ በሕጻንነት መመንኮስ ነው ብለናል ይህንንም ስንል በአየነው ተጨባጭ መረጃ እንጂ እንዲሁ ለማስመሰል አይደለም ቢያስፈልግም በሕፃንነታቸው መንኩሰው ያፈረሱ ብዙዎች ወጣት መነኮሳትን አንድ ሁለት ብሎ መቁጠርና ስም ስማቸውን መጥራት ይቻላል ። ለምን እንዲህ አደረጋችሁ ተብለው ሲጠየቁ ግን አብዛኞቹ የሚሰጡት መልስ የመነኩስነው በሕጻንነታችን ወራት ስለሆነ ቀድሞም ቢሆን ይህን ከባድ ሸክም የተሸከምነው አስበንበትና ጉዳዩን ተረድተን ስላልሆነ አሁን ምርጫችንን ማስተካከል ይገባናል » የሚል ነው ይህ አባባል ትክክል ነውን ስንል ግን መልሱ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ » እንደሚባለው ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ግን ይህን የመሰለው ምክንያት ትክክለኛ መስሎ የሚታይበት ጊዜ ያለ ይመስላል ለምን? ቢባል በ14 በ15ና በ16 ዓመታቸው የመነኩሱ ብዙ ወጣቶች ስላሉ ነው ታዲያ እንደነዚህ ያሉት ወጣቶች በእድገና አካለመጠንበደረሱ ጊዜ ራሳቸውን መግታትና የሰይጣንን ፈተና መቋቋም እጅግ ያዳግታቸዋል ።

ከዚህም የተነሣ « መኑ የአቁር እሳተ ውስተ ሕጽኑ » የሚለውን ጥቅስ እየጠቀሱ ወደ ስርቆት ያመራሉ ቀስ በቀስም እየተለማመዱ ትሲሄዱ ኃጢአት እንደጽድቅ ስለሚቆጠር በሥውር የጀመሩትን ሥርቆት በገሐድ በማውጣት ቆባቸውን አውልቀው ከአባትነት ወደ አቶነት ይመለሳሉ ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በወጣትነታቸው መንኩሰው በገዳም ውስጥ ሥርዓተምንኩስናን እያጠኑ ከማደጋቸው የተነሣ ለመንፈሳውያን ተግባራት አብነት የሆኑና ንጽሕናቸውን ጠብቀው ለቅድስና የበቁ ብዙ አባቶች ስላሉን በወጣትነት ዘመናቸው የመነኩሱት ሁሉ በዚህ መጥፎ ዓላማ ተመርተዋል ለማለት እንዳልሆነ በግልጥ መታወቅ አለበት ግን በአንዳንድ ግለሰቦች ምክንያት ያደፈውን የምንኩስና ታሪክ ለማደስ መፍትሔው ሰው ሁሉ በቅድሚያ ምርጫውን አስተካክሎ እንዲመነኩስና ዓላማውን ጠብቆ ለመኖር እንዲችል ማድረግ ተገቢ መሆኑን ለመጠቆም ነው ይህም ችግር ሊቃለል የሚችለው በ14 በ15 በ16ና በ17ዓመት የሚመነኩስትን ወጣቶችእያስተማሩ ቢያንስ እስከ 25 ዓመት ዕድሜያቸው ድረስ አቆይቶ አመክራቸውን ሲጨርሱና በራሳቸው መተማመን ሲችሉ እንዲመነኩሱ ሲደረግ ነው ።

አንድ ወጣት ለምስክርነት የሚበቃው ለመክሰስም ሆነ ለመከሰስ ሙሉመብት ትኖሮት ያለሞግዚት በሕግ ፊት ለመቆም የሚችለው ቢያንስ ከ18ዓመት በላይ ዕድሜ ሲኖረው መሆኑ በሕግ የታወቀ ነው።

በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10 ላይ መመንኮስ የሚገባቸው ሰዎች እንዴት ያሉ እንደሆኑ ተገልጧል ። በዚህም መሠረት » አንድ ሰው ሊመነኩስ ወደ ገዳም በሚመጣበት ጊዜ ራሱን ያልቻለ ወጣት ቢሆን አያመንኩሱት » በማለት ራሳቸውን ያልቻሉ ወጣቶች መመንኮስ እንደማይገባቸው ከማስረዳቱም ሌላ የገዳሙ አበ ምኔት ሰዎችን ከማመንኩሱ በፊት ሊወስድ ስለሚገባውጥንቃቄ ሲያስረዳ ማንኛውም ሰው ሊመነኩስ በሚመጣበት ጊዜ የገዳሙ አበ ምኔት ብርቱ ምርመራ በማድረግ ከወዴት እንደመጣ ፣ ሥራው ምን እንደነበረ በምን ምክንያት ለመመንኮስ እንዳሰበ ፣ ምናልባትም የሚረዳቸው እናት አባት ወይም ሚስትና ልጆች እንዳሉትና እንደሌሉት በጽኑዕ ይመረምረው » ይልና ምናልባት በችግር ምክንያት ቤተሰቡን ለመሸሽ ከሆነ አያመንኩሱት » በማለት ያትታል ። ታዲያ የምንኩስና ሕግ ቀላል ስላልሆነ ከባድ ጥንቃቄም የሚጠይቅ መሆኑ እየታወቀ የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ በሆነው በፍትሕ መንፈሳዊም በሚገባ የተደነገገ ሲሆን ሁኔታውን ሳይመረምሩ በአመክሮም ሳይፈተኑ ለሚመጣው ሁሉ ቆብ እየባረኩ የሚጭኑና የሚያመነኩሱ የገዳማት አበ ምኔቶች ቢኖሩ ችግሩን ተገንዝበው ከባድ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ



ዲያቆን በሱ ፈቃ... ዓ.ም. በታዕካ ነገሥት
በዓታ ለማርያም ...



www.ethiopianorthodox.org